# "ጌታ እንዲህ ይላል"

# የሚለዉን ብቻ እመን

በኢ. ፍራንክ



እ.ኤ.አ. የካቲት 28/1963 ይህ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ደመና በአሪዞና በሚገኘው ሰንሴት ተራራ አቅራቢያ ታየ ፤ ይህም ቀደም ሲል ለሬቨረንድ ብራንሃም በታህሳስ 22/1962 በራዕይ እንደታየው ነው። ይህ ሥዕል ክርስቶስ ባዓረገ ጊዜ በደመና እንደተወሰደ ያስታዉሰናል (ሐዋ.1:9)። በተመሳሳይ መንገድ ይመለሳል (ቁ.11)። ይህ የእርሱ በቅርብ የመምጣት ምልክት ሊሆን ይችላልን? ምንም እንኳን ይህ ሥዕል የተነሳዉ ከሩቅ ቢሆንም፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ጋር መመሳሰሉ በግልጽ ይታያል።

“ሳይንስ “ መጽሔት፣ እ.ኤ.አ ሚያዚያ 19 ቀን 1963 እትሙ  በዚህ ክስተት ላይ አንድ ጽሑፍ አዉጥቷል እንዲሁም ሥዕሉንም በፊተኛዉ ሽፋኑ ላይ ይዞ ነበር። ከታላላቅ ሳምንታዊ ህትመቶች አንዱ የሆነው “ላይፍ” መጽሔት፣ ግንቦት 17 ቀን 1963 ዓ.ም. ካቀረበዉ ዘገባ ጋር የዚህን ደመና ፎቶግራፍ አትሞታል። የዚህ ምስጢራዊ ደመና ክስተት በሳይንቲስቶች ሊብራራ አልቻለም። ደመናው በሰማያዊው ሰማይ ላይ ከፍ ባለ ከፍታ ላይ ተንጠልጥሎ ነበር፣ ይህም እርጥበት ደመና ለመፍጠር ከሚያስችለው ከፍታ እጅግ የላቀ ነበር። ለነብዩ የተሰጠውን ተልዕኮ የሚያረጋግጥ ከሁሉን ቻይ አምላክ የተሰጠ እንዴት አይነት ማረጋገጫ ነው ! ጌታ እግዚአብሔር ተናግሯል፣ የማይሰማስ ማን አለ!

# መቅድም

የዊልያም ብራንሃም (1909—1965) ክስተት በራሱ ልዩ ትኩረት የሚይስብ ብቻ ሳይሆን በዘመናዊው ዓለምም ውስጥ ተወዳዳሪ የለዉም። በዚህ ሰው አገልግሎት እግዚአብሔር በዘላለማዊ ዕቅዱ ውስጥ ምን ለማከናወን እንዳሰበ ራሳችንን መጠየቅ የለብንም?

በግለሰብ ደረጃ፣ ወንድም ብራንሃም በግልጽ ሰው ብቻ ነበር — ግን በጣም የሚወደድ ሰው ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅባት በእርሱ ላይ አረፈ። እርሱም እግዚአብሔር በጥንት ነቢያቶቹ ላይ እንዳደረገው ሁሉ፣ በመለኮታዊ ትክክለኛነት ሁልጊዜ የሚያረጋግጠዉ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚል ነበረው። ወንድም ብራንሃም በእግዚአብሔር ሥር ሆኖ የሕይወት ጌታ እየሱስ ለሐዋርያት አስቀድሞ የሰጣቸዉን ህሙማንን የመፈወስ እና ሙታንን የማስነሳት ተመሳሳይ ሃይል ተግባራዊ አድረጓል (ማቴ. 10:1—8)። በጸሎቱ አማካኝነት ከካንሰር፣ ከዓይነ ስውርነትና ከሁሉም ዓይነት በሽታዎች መዳናቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ምስክሮች ያረጋግጣሉ።

ነገር ግን አገልግሎቱ በምንም ሁኔታ ቢሆን የታመሙትን በመፈወስ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ለዚህ ለመጨረሻዉ ዘመን ትውልድም መልእክት አመጣ፤ የክርስቶስ ሙሽራ በዚህ በመጨረሻዉ ዘመን ራሷን እንድታዘጋጅ የሚያግዝ መገለጥ። ሐዋርያት ከኖሩበት ጊዜ ጀምሮ፣ ወንድም ብራንሃምን ያህል በተቀደሰ ሕይወቱ፤በትምህርቱ ወይም በአገልግሎቱ ጌታ ኢየሱስን ያከበረ ሰው የለም መባሉ እውነት ነው ብዬ አምናለሁ። ጌታ ራሱ እንዲህ በሚያረጋግጥበት ጊዜ፣ የጌታ አገልጋይ የሰዎች ማረጋገጫ ያስፈልገዋልን?

ስለዚህ ይህ የወንድም ፍራንክ መጽሐፍ የወንድም ብራንሃምን ትክለኝነት ለማረጋገጥ የተደረገ ሙከራ አይደለም፣ ነገር ግን የተጻፈዉ የእውነት

ፈላጊዎችን ለመርዳት ፣ በተለይም የዚህን ሰው ሕይወትና አገልግሎት በትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ አውድ ውስጥ ማስቀመጥ ለሚፈልጉት ነዉ:: ተቃዋሚው፣ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማበላሸት በሚያደርገው የማያቋርጥ ጥረት፣ እዚህም እንደሌሎች ስፍራዎች ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ልጆች መካከል አለመግባባትንና ግራ መጋባትን ለመዝራት ሞክሯል::

ወንድም ፍራንክን ለብዙ ዓመታት ማወቄ ለእኔ መልካም አጋጣሚየ ሆኗል:: እርሱ አገልግሎቱ ከ100 በሚበልጡ አገሮች ውስጥ ወደ ሁሉም አህጉራት የወሰደው አገልጋይ ነው:: ከሁሉም አውሮፓውያን ወንድም ፍራንክ ፤ ወንድም ብራንሃምን በደንብ ስለሚያውቅ እና እግዚአብሔር የሰጠውን አገልግሎቱን ለብዙ ጊዜ የቅርብ ልምድ ስላለው፣ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ በጣም ብቁ ሊሆን ይችላል:: በተመሳሳይ ጊዜ፣ በጂኦግራፊያዊ አነጋገር፣ በብዙዎች ዘንድ ጠቃሚ ሊሆን የሚገባውን የዚህን አገልግሎት ሚዛናዊና ገለልተኛ ፍርድ ለመመስረት ከአሜሪካ ማዕከላዊ ነጥብ በበቂ ሁኔታ ርቆ ነበር:: ይህ የማብራሪያ ሪፖርት ለብዙዎች በረከት ይሁን::

ፕሮፌሰር ዶር ሊዮን ሎንግ

የጆፈርሰንቪል፣ ኢንዲያና፣ ዩናይትድ ስቴትሱ ወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በመላው ዓለም በደንብ የታወቀ ነው:: በብዙዎች የተከበረና የተወደደ ነበር፣ ሌሎቹ ደግሞ እርግጥ ነዉ በስህተት ተረድተዉት ነበር:: የዚህ ትሁት የእግዚአብሔር ሰው አገልግሎት ስንት ሚሊዮኖችን እንደባረከ ዘላለማዊነት ብቻ ነው የሚገልጸው::



በክርስቶስ የተወደዳችሁ ሆይ፣ እግዚአብሔር የሚያደርገው ሁሉ በቤተክርስቲያናችን፣ በከተማችን ወይም በሀገራችን ላይ ላይሆን ይችላል:: እግዚአብሔር የሆነ ነገር ሲያደርግ ሁልጊዜ እዚያ ልንሆን አንችልም፣ ነገር ግን ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ክስተቶችን አይተው ሊመሰክሩልን ለሚችሉ ምስክሮች በእርግጠኝነት አመስጋኞች ነን:: ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ቆሞ የተወደደውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያጠምቅ እኔ እዚያ አልነበርኩም:: ነገር ግን ነቢዩ የእግዚአብሔርን በግ ሲያጠምቅ ከተፈጥሮ በላይ ስለተከሰተው ክስተት እና ድምፅ ከሰማይ እንደተሰማ በሚገልጸው ዘገባ አምናለሁ::

ምናልባት ወንድም ብራንሃም እ.ኤ.አ ሰኔ 11/1933 በኦሃዮ ወንዝ ላይ ቆሞ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሲያጠምቅ እርስዎ እዚያ ያልነበሩ ይሆናል:: 17ኛውን ሰው ሊያጠምቅ ሲል እንዲህ ብሎ ጸለየ፦ “አቤቱ፣ እኔ በውኃ እንደማጠምቅ፣ እንዲሁ አንተም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት አጥምቅ ::” በዚያን ጊዜ ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ደማቅ የሚያብረቀርቅ የብርሃን ምሰሶ ፣ በግምት 4,000 ሰዎች እያዩት ወንድም ብራንሃም ላይ ወረደ፣ እናም ድምፅ ተሰማ፦ “ መጥምቁ ዮሐንስ የክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ቀዳሚ ሆኖ እንደተላከ ሁሉ ፣ አንተም እንዲሁ የክርስቶስን ሁለተኛ ምጽአት የሚቀድም መልእክት ይዘህ ተልከሃል::”

ብዙዎች የተወሰኑ ልምዶች እንዳላቸው የሚናገሩ መሆናቸውን በሚገባ አውቃለሁ፣ በዚህም ምክንያት ሰዎች በጥርጣሬ ተሞልተዋል:: ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን፣ በእነዚህ ሰው ሰራሽ እና በተፈበረኩ ተብዬ ልምዶች መካከል፣ ከእግዚአብሔር እውነታ ጋር በዚህ ትዉልድ ፊት ለፊት ተገናኝተናል:: ይህ የእግዚአብሔር ታላቅ ጉብኝት ሲከሰት እዚያዉ የነበሩትን እኔ በግሌ 15 የሚያህሉ ሰዎች አይቻለሁ:: እንግዲህ፣ ወንድም ብራንሃም የተናገረውን እና ምስክሮቹ የመሰከሩትን ማመን ካልቻልን፣ እንግዲያስ ይህን ሰው በመላው ዓለም ትክክለኝነቱን ያረጋገጠለትን እግዚአብሔርን እመኑ::

ሁሉም ሰዉ ሙሴ፣ አብርሃም፣ ዮሐንስ ወይም ጳውሎስ ሊሆን አይችልም፤ ሁሉም ወንድም ብራንሃምም ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር በአንድ የተወሰነ ጊዜ ወይም ዘመን ያዘዘውን ለማድረግ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሰው መሆን ይጠይቃል። በእርግጠኝነት የኢየሱስ ቃላት ለዘላለም እውነት ናቸው፦ "ነቢይን የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይቀበላል (ማቴ. 10:41)።" በእግዚአብሔር የተላከ ነቢይን የሚያምኑ ሁሉ በዚያ ቀን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ጸድቀው ይቆማሉ እና ሽልማታቸውን ከዚያ ነቢይ ጋር ይቀበላሉ።

ጊዜዉ እያለቀ ነዉ ። በማቴ. 25:6 ያሉትን የኢየሱስን ቃላት እናስታውሳለን፡- "በእኩለ ሌሊትም፦ እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፤ ልትቀበሉት ውጡ! የሚል ጩኸት ሆነ።" ጌታ ከነዚህ ቃላት ቀደም ብሎ በማቴ. 24:45 ልንዘነጋው የማይገባ ነገር ተናግሮ ነበር፦ "እንግዲህ ጌታው በቤተሰቦቹ ላይ የሾመው፣ በጊዜውም ምግባቸውን የሚሰጣቸው ታማኝና አስተዋይ አገልጋይ ማን ነው?" እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይና ነቢይ በጊዜው ምግብ እንዲሰጥ በጌታ ቤት ላይ ተሹሟል። የዮኤልን ትንቢትም ያስታውሰናል፦ ".. ዓመታትን ሁሉ እመልሳለሁ ይላል ጌታ..." (ኢዩኤል 2:25)። ጌታ ቃሉን እንደጠበቀ ግልጽ ነው። እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ የቃሉ ግልጽ ትምህርት፣ ተመልሷል።

ይህ ነቢዩ ኤልያስ ሁሉንም ነገር ለመመለስ እንደሚላክ የተነገረውን ትንቢት ያስታውሰናል። ሌላ ሳይሆን ይህ ታላቅ ነቢይ  የተጠቀሰዉ ለምንድን ነው ? እባክዎ 1ኛ ነገሥት 18ን በጥንቃቄ ያንብቡ። በቁጥር 21 ላይ ነቢዩ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል እናገኛለን፦ "እስከ መቼ ድረስ በሁለት ሐሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ከሆነ ተከተሉት።" በ30ኛው ቁጥር ደግሞ እንዲህ ይላል፦ "ወደ እኔ ቅረቡ። ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡ። ፈርሶ የነበረዉንም የእግዚአብሔርን መሠዊያ ሰራ።" ኤልያስ ለዚያ ሰዓት የእግዚአብሔር ቃል ነበረው። በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሰዎችን ሰበሰበ። ከዚያም እንደ እስራኤል ነገዶች አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ወስዶ መሠዊያውን አደሰ። ይህ ከተደረገ በኋላ ብቻ ጌታ በእሳት ሊመልስና ዝናብም ሊያወርድ ችሏል።

በዚህ ጊዜ ብዙዎች ለመንፈሳዊ ዝናብ ጸልየዋል እና ብዙዎች ጌታ በእሳት መለሰ ብለው ተናግረዋል። በመጀመሪያ ደረጃ፣ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ የአሥራ ሁለቱን ሐዋርያት እውነተኛ ትምህርት አንስቶ **ቃሉን ለቤተክርስቲያኑ** ሊመልስ የሚችል ነቢይ መላክ ነበረበት። በጌታ ቤት ውስጥ ያለው መሠዊያ በእርሱ የማስተማር አገልግሎት አማካኝነት ታድሷል። አሁን ሕይወታችንን በእርሱ ላይ ልናስቀምጥ እንችላለን፤የእግዚአብሔር ቃልን በሙሉ ልባችን እያመንን።

ውድ የሆነዉን የእግዚአብሔርን ቃል በአለም ዙሪያ ላሉ ውድ የእግዚአብሔር ልጆች ማካፈለን እንደ ትልቅ እድል እቆጥረዋለሁ። ይህ

ህትመት፣ የወንድም ብራንሃም ስብከቶች እንደተደረጉት ሁሉ፣ ወደ ብዙ ቋንቋዎች ይተረጎማል። ብቸኛው ዓላማ የብዙዎችን ትኩረት ወደ እግዚአብሔር ቃል እንዲሳብ ማድረግ ነው። እባክችሁ መልእክቱንም ሆነ መልእክተኛውን ከማወቅ አትቆጠቡ። ይህን መጽሐፍ በሚያነቡበት ጊዜ 2ኛ ጴጥሮስ 1:19ን እያሰቡ ይሁን ፦ “ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ቀኑም እስኪጠባ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፤ሰዉ በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ።”

ጌታ ሁላችሁንም ይባርካችሁ እና ይህን ማብራሪያ በትክክል እንድትረዱ ይስጣችሁ። Bro. Frank

## “ጌታ እንዲህ ይላል” የሚለዉን ብቻ እመኑ

**ጌታ እንዲህ ይላል** የሚሉት ቃላት ለብዙዎች አዲስ ትርጉም ሁነዋል። የእግዚአብሔር ነቢያት፣ በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስተው፣ ሁልጊዜም “**ጌታ እንዲህ ይላል**” ለማለት ችለዋል። የወንድም ብራንሃምን ትንቢታዊ አገልግሎት የተመለከቱት፣ እርሱ “**ጌታ እንዲህ ይላል**” ሲል በመንፈስ ቅዱስ እንደተነሳሳ እና በመለኮታዊ መገለጥ ላይ እንደተመሰረተ በእርግጠኝነት መቀበል አለባቸው።

እየኖርን ያለነዉ ብዙ ነገሮች እየሆኑ ባሉበት እና ዜናው ቀጥሎ ምን እንደሚያመጣ እያሰጋን ባለበት ዘመን ውስጥ ነው። ፓስተሮችና ወንጌላውያን ሁሉንም ነገር ለመረዳትና በትክክል ለማብራራት እየሞከሩ ነው። እየተከናወኑ ያሉትን የዓለም ክስተቶች በተሻለ ለመረዳት በማሰብ ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ሆኖም፣ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት እጅግ በቀረበበት በዚህ ጊዜ በሚገባ የታሰቡት የሰው ትርጓሜዎች አያስፈልጉንም። የሚያስፈልገን በማይሻረዉ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ የእውነተኛ ነቢይ **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚል ቃል ነው። በዚህ በመጨረሻ ዘመን ላይ የተነገሩት ትንቢቶች ፍጻሜያቸውን እያገኙ ባሉበት ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው። ማንም ሰው መለኮታዊ ነገሮችን ከሰው አመለካከት ተነስቶ የመተርጎም መብት የለውም። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ሊታወቁና ሊገለጡ ይችላሉ። ጌታ እግዚአብሔር በነቢያቱ አፍ ትንቢቶችን እንደተናገረ ሁሉ፣ በፍጻሜው ጊዜም ትርጉማቸውን እንዲሁ አስታወቋል።

ዓላማችን ወንድም ብራንሃምን ወይም እግዚአብሔር የሰጠውን አገልግሎት ለመከላከል አይደለም። እግዚአብሔር ለ33 ዓመታት እንዲህ ያሉ ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን ሊሠራበት የቻለ ሰው የማንም ጥብቅና አያስፈልገውም። በዚህ ትውልድ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ካጋጠሟቸው መካከል፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ዓለምን ያጥለቀለቀውን ታላቅ መነቃቃትን(ሪቫይቫል) ለመምራት እግዚአብሔር ወንድም ብራንሃምን በልዩ መንገድ እንደተጠቀመበት የታወቀ እውነታ ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ባይሆን ኖሮ ማንም ሰው የተከሰቱትን ነገሮች ሊያደርግ አይችልም ብለን በእውነት መናገር እንችላለን። ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በቅርበት ከመመልከታችን በፊት፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተመዘገበውና አስቀድሞ በተነገረው የመዳን ዕቅድ መሠረት እንደሚያደርግ መገንዘብ አለብን።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር ሰው ስለ ድነት ዕቅድ የሚመለከቱ ነገሮችን ለመናገር ወይም ለመጻፍ በተመረጠበት ጊዜ ሁሉ፣ ሁልጊዜም ወደ ትንቢታዊው ቃሉ ተመልሶ ይጠቅስ ነበር። የአራቱም ወንጌላት ጸሐፊዎችና ሐዋርያት ያደረጉት ይህ ነው። እግዚአብሔር በተወሰኑ ጊዜያት በእያንዳንዱ ዘመን እንዲሆኑ የታዘዙትን ነገሮች ለመፈጸም ሰዎቹን እንደመረጠ መቀበል አለብን። ያኔ እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን ትምህርት በትንቢታዊው ቃል ጌታ

**እንዲህ ይላል** ላይ የተመሠረተ ነው ብሎ በእውነት መናገር ይቻላል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዲጽፉ ወይም እንዲናገሩ የተመረጡት የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ነቢያት እንደነበሩት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስተው ነበር። ሁልጊዜም አስቀድሞ በመንፈስ ቅዱስ ተነግሮ ወደተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ተመልሰዉ ይጠቅሱ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለዉ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ በትንቢታዊው ቃል ብርሃን ተመለሰ እና ከዚያም **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚል ሆነ። ይህ የሰው መልስ ሳይሆን፣ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር በቃሉ መሠረት የሰጠዉ መለኮታዊ መልስ ነበር። ስለዚህ፣ ጴጥሮስ በ2ኛ ጴጥሮስ 1:21 ላይ የጻፈውን መረዳት እንችላለን፦ "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እየተነዱ ተናገሩ።" በተመሳሳይ መንገድ፣ የእግዚአብሔር ሰዎች በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው፣ የተፈጸሙትን ትንቢቶች የምስራች አወጁ። በሮሜ 1:1-2 ጳውሎስ የሚጽፍበትና የሚገነባበትን መሠረት ያስቀምጣል፦ "የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የሆነ ጳውሎስ፤ ሐዋርያ ለመሆን የተጠራ፤ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። ይህም ወንጌል ቀድሞ በነቢያቱ አማካኝነት በቅዱሳት መጻሕፍት ተስፋ ተደርጎለት ነበር።" ሐዋርያው እዚህ ላይ የወንጌል ተስፋ ቀድሞ በቅዱሳት መጻሕፍት በነቢያት እንደተጻፈ ይናገራል።

ወደ ሮሜ ሰዎች ወይም ወደ ዕብራውያን ሰዎች መልእክትን ስናነብ፣ በአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ውስጥ የትንቢታዊው ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** ምን ያህል ጊዜ ጥቅም ላይ እንደዋለ እናያለን። በሮሜ 9:24-26 ላይ ጳውሎስ የአሕዛብን መለወጥ በቅዱሳት መጻህፍት ይሚገታል፡-"...ከአህዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን፡፡ እንዲሁ ደግሞ በሆሴዕ ፡- ሕዝቤ ያልሆነዉን ሕዝቤ ብየ ፤ ያልተወደደችዉንም የተወደደችዉ ብዬ እጠራለሁ ፤ እናንተ ህዝቤ አይድላችሁም በተባለላቸዉም ስፍራ በዚያ የሕያዋን እግዚአብሔር ልጆች ተብለዉ ይጠራሉ ይላል ፡፡ "

ጳውሎስ ተመሳሳይ ጉዳይ ሲመለከት በሮሜ 15:9-11 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "...አሕዛብም ስለ ምሕረቱ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ እንደ ተጻፈም፦ በዚህ ምክንያት በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ፤ ስምህንም እዘምራለሁ። ደግሞም፡- አሕዛብ ሆይ፤ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ! ይላል። ደግሞም፤ አሕዛብ ሆይ፡- ጌታን አመስግኑት፤ ሕዝቦችም ሁሉ አሞግሱት! ይላል።"

ጳውሎስ ትምህርቶቹን በጌታ ነቢያት በተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ላይ እንደመሠረተ በግልጽ እናያለን። እንደ ሐዋርያት ሥራ 15:13-15፣ ይህ በኢየሩሳሌም በነበሩ ሐዋርያት መካከል ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር የውይይት ርዕሰ ጉዳይ ነበር። እንዲህ ሲል እናነባለን፡- "ዝም ካሉ በኋላም ያዕቆብ እንዲህ ብሎ መለሰ፡- ወንድሞች ሆይ፤ ስሙኝ። እግዚአብሔር ለስሙ የሚሆንን ወገን

ከአህዛብ ይወስድ ዘንድ አስቀድሞ እንዴት እንደጎበኘ ስምዖን ተርኳል ። ከዚህም ጋር የነቢያት ቃል ይስማማል ፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ...”

ጳውሎስ ብቻ ሳይሆን፣ ያዕቆብም ቅዱሳን ነቢያት ወደ ተናገሩት ቃላት ተመልሶ ሲጠቅስ እናገኛለን። የአንድ የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅስ መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሊገኝ እንደሚችል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መማር አለብን። በሮሜ 15:4 ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “በመጽናት መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈዉ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፏልና ።”

ወደ ተጻፈዉ የእግዚአብሔር ቃል መመለስን መማር እና በዚህ መሰረት **ጌታ እንዲህ ይላል** በሚለዉ መልሳችንን ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። ጳውሎስ፣ ያዕቆብ እና የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ትክክል ነው ብለው ያሰቡትን መልስ እንዳልሰጡ እናያለን፣ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው መልሱን ከእግዚአብሔር ቃል ሰጡ።

በሐዋርያት ሥራ 8:35 ላይ ግሩም የሆነውን አባባል እናነባለን፦ “ፊልጶስም አፉን ከፈተ፤ ከዚህም መጻህፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት።” እስጢፋኖስም በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነበር። በሐዋርያት ሥራ 7 ባለው ስብከቱ፣ ብዙ ጊዜ ወደ ትንቢታዊው ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** ይጠቁማል። ብሉይን ከአዲስ ኪዳን መለየት አይቻልም። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ተሰጥተዋል በአዲስ ኪዳንም ተፈጽመዋል። የምንሰብከውና የምናስተምረው ሁሉ በተሟላው የእግዚአብሔር ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር ቃል ዓላማ የራሳችንን ሃሳቦችና ትርጓሜዎች መጨመር ሳይሆን፣ የመዳንን ዕቅድ በትንቢታዊው ቃሉ መገለጥ እንድናይ ነው። ለዚሁ ዓላማ፣ እግዚአብሔ ቃሉን በጌታ እዉነተኛ መነሳሳት እንዲናገሩ ከጥንት ጀምሮ ሰዎቹን መርጦ ነበር ።

ከተሐድሶዉ ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር አንድን እዉነት ከሌላዉ እዉነት ቀጥሎ ወደ ነበረበት ከእግዚአብሔር ቃል እንደመለሰና እንደገለጠ ማየት እንችላለን። በእያንዳንዱ ዘመን፣ በእግዚአብሔር የተላከውን መልእክተኛ የተቀበሉ እና በጌታ ስም የተነገረውን የሰሙ፣ የእግዚአብሔርን በረከት ተቀብለዋል። የስአቱን መልእክት ያመኑ እነርሱ የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ነበሩ። በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዳደረጉት፣ አሁን እየሆነ ያለውን ሁሉ በትንቢታዊው ቃል ብርሃን ማየት አለብን።

በማቴ. 1:22-23 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፦ “በነቢይ ከጌታ ዘንድ ፦ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ፤ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለዉ ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል ፤ ትርጓሜዉም ፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነዉ ።”

ማቴዎስ በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስቶ ነበር፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ ወደተሰጠው ትንቢታዊ ቃል ተመለሰ። ሰባ ሰገል ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ክርስቶስ የተወለደበትን ቦታ ሲጠይቁ፣ መልሳቸውንም ከእግዚአብሔር ቃል ተቀበሉ። በማቴ. 2:5-6 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፡-"እነርሱም ፡- አንቺ ቤተልሔም፤ የይሁዳ ምድር ፤ ከይሁዳ ገዥዎች ከቶ አታንሽም ፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንች ይወጣልና ተብሎ በነብይ እንዲህ ተጽፏልአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነዉ አሉት።"

በማቴ. 26:31 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ ፤ እረኛዉን እመታለሁ የመንጋዉም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፏአልና ፤"

ክርስቶስም ያለማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር ቃል እየተመለሰ እንደጠቀሰ እናያለን። በማቴ. 26:54 ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "እንዲህ ከሆነስ ፡- እንደዚህ ሊሆን ይገባል የሚሉ መጻህፍት እንዴት ይፈጸማሉ?"... " ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነዉ የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ነዉ አለ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ እርሱን ትተው ሸሹ።" (ቁ. 56)። የዚህን ርዕስ ጥናት ብናደርግ፣ ሐዋርያት የነቢያትን ቃል ምን ያህል ጊዜ እንደጠቀሱ ስናይ እንገረማለን።

ማር. 1:1-2 እንዲህ ይላል፦ "የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ። በነብዩ በኢሳያስ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል "እነሆ መንገድህን የሚያዘጋጅ መልእክተኛየን በፊትህ እልካለሁ ፤ " ማርቆስ ለወንጌሉ በትንቢታዊ ቃሎች ላይ መሰረት ሲጥል ትኩረታችንን ነቢያቶች ወደ ሆኑት ሚልክያስ (3:1) እና ኢሳይያስ (40:3) ወዲያዉኑ ይመራዋል። እርሱ **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለውን አጽንዖት በመስጠት እግዚአብሔር በነቢያት ቃል የገባውን ፍጻሜ ያሳያል። በአራተኛው ቁጥር፣ ማርቆስ ቀዳሚዉን በመጥቀስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ።" ዮሐንስ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር የተላከ መልእክት ያለው በእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ ነበር።

ለእግዚአብሔር ቃል ቅድሚያ መስጠት ትልቅ ትርጉም እና ጠቀሜታ ያለዉ ነዉ። ማርቆስ በትንቢታዊው ቃል መሠረት ካስቀመጠ በኋላ፣ ስለ ዮሐንስ የበለጠ ይነግረናል። ተልእኮውና መልእክቱ ተገልጿል። ነቢዩ እንዴት ይለብስ እንደነበርና ምን ይበላ እንደነበር ይጠቅሳል። ማርቆስ ስለ ኢየሱስ ማውራት ያቆም እና ስለ ቀዳሚዉና ነቢዩ ማውራቱን ይቀጥላል። ይህ በጣም አስደናቂ ነው።የኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ቀዳሚ መጥቶ አስደናቂ ምስክርነት ትቶ ሄዷል። በእነዚህ የመጨረሻ ቀናት፣ በእኛ መካከል፣ በርካታ የመጨረሻ ዘመን ትንቢቶች የተፈጸሙበትና በአሁኑ ጊዜም እየተፈጸሙበት ያለ ድራማ እየተከናወነ ነው። ልክ እንደ ዮሐንስ፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም

ምጽአትም ቃል የተገባለት ቀዳሚ(የሚያዘጋጅ) አለ:: ይህ እውነታ በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ከመጻህፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በማሳየት የበለጠ ይረጋገጣል::

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለጌታ የመጀመሪያ ምጽአት ቀዳሚ የሚናገሩ ከሆነ፣ እንግዲያስ ስለጌታ ሁለተኛ ምጽአት ቀዳሚም በእርግጠኝነት መጻፍ እንችላለን:: የእግዚአብሔር የተሟላ የመዳን ዕቅድ በቀደመዉ እዉቀቱ አስቀድሞ ተወስኗል፣ ለእያንዳንዱ ዘመንም መልእክትና መልእክተኛውም እንዲሁ:: መልእክቱን የሚሰሙ ሰዎችም ቢሆኑ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በእግዚአብሔር አስቀድመው ተወስነዋል::

እኛ **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለውን መሠረታችን እንዳደረግን እናረጋግጣለን:: በእርግጥ ዮሐንስ በእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ መሆኑን ያላመኑት ጸሐፍት ማርቆስ በጽሑፉ  እርሱን መጥቀሱ አናዷቸዉ ሊሆን ይችላል:: በእርግጥም ሰውን በማክበሩ ሊከሱት ይችሉ ነበር፣ ነገር ግን ማርቆስ በመንፈስ ቅዱስ ተነሳስቶ ነበር:: የተከናወነውን ነገር ከእግዚአብሔር ቃል በተገለጠው  በፍጹም እርግጠኝነት መጻፍ ችሏል::

የተወደዳችሁ ሆይ፣ እግዚአብሔር በዚህ ትውልድ ቃል የገባውንና የፈጸመውን በመንፈስ ቅዱስ ለተሞሉ ሰዎች መካድ  አይቻልም:: በእግዚአብሔር ጸጋ ወደ **እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ተመልሰናል:: አሁን የትንቢታዊውን ቃል አስፈላጊነት በኢየሱስ ክርስቶስ መግለጥ ብርሃን መረዳት እንችላለን::

አሁን ወደ ጥያቄው እንምጣ :- ጸሐፍት በዘመናቸው የትንቢቶችን ፍጻሜ ያልተገነዘቡት ለምንድን ነው? በቀላሉ የራሳቸውን የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ስላቋቋሙና እግዚአብሔር ቃሉን በራሳቸው ትርጓሜ መሠረት እንዲፈጽም እየተጠባበቁ ስለነበር ነው::  በዚህ ትውልድ ላሉ ጸሕፍትም እንደዛዉ እየሆነ ነው::

**ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለዉን ትንቢታዊ ቃል የሚረዱ ብቻ በዚህ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት እየተፈጸሙ መሆናቸውን ይገነዘባሉ:: እግዚአብሔር ከክርስቶስ መጀመሪያው ምጽአት በፊት ነቢይን እንደላከ ሁሉ፣ የዳግም ምጽአቱም ቀዳሚ ነቢይ ነበረው:: በሰው አስቀድሞ በተያዙ ትርጓሜዎች መካከል ቆሞ፣ በመንፈስ ቅዱስ መገለጥ አማካኝነት፣ የእግዚአብሔርን ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለውን በዚህ ትውልድ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሆኑ አመጣ:: ሁሉንም ሰው ሰራሽ የሆኑ ትርጓሜዎችን ትተን ወደ እግዚአብሔር ቃል የምንመለስበት ጊዜ አሁን ነዉ::

በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሆነው ነገር ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ነበር ማለት እንችላለን:: ልደቱ፣ ሕይወቱ፣ አገልግሎቱ፣ መከራው፣ ሞቱ፣ ትንሣኤው እና ዕርገቱ ሁሉም እንደ እግዚአብሔር ቃል ነበር:: ሁሉም

በእግዚአብሔር ነቢያት በተነገሩት የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሠረት ተፈጽሚል። የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ላይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እየሆነ ያለዉ ሁሉ በእግዚአብሔር አስቀድሞ በተወሰነው ምክር መሠረት እንደሆነ እናያለን።

በሉቃስ 4:16 ላይ ጌታ ኢየሱስ በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ እንደገባና የነቢዩ ኢሳይያስ መጽሐፍ እንደተሰጠው እናነባለን። ከምዕራፍ 61 አስደናቂውን ክፍል አነበበ፣ ይህም በዚያን ጊዜ ከአገልግሎቱ ጋር የተያያዘ ነበር፣ እናም የሚከተሉትን ቃላት መናገር ጀመረ፡- "ዛሬ ይህ መጻህፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ። "

እንዳየነው፣ ጸሐፊዎችም እንደ ጌታ ክርስቶስ የትንቢቶችን መፈጸም በተደጋጋሚ አጽንዖት ሰጥተዋል ። በክርስቶስ የተወደዳችሁ ሆይ! በዚህ ጊዜ ትኩረቱ የት ላይ እንደሆነ ተገነዘብን? ጌታ ኢየሱስና በአዲስ ኪዳን ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ሁልጊዜ ወደ ብሉይ ኪዳን ተመልሰዉ ይጠቅሱ እንደነበር ተረድተናል? እየተከናወነ ያለው ነገር ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሆነ ያለማቋረጥ አስረድተዋል። ሁሉን ቻይ በሆነዉ በእግዚአብሔር ጸጋ በትክክል እያደረግነዉ ያለነዉ ይህንን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ሲፈጸሙ የማየት እና እግዚአብሔር በዘመናችን ስላደረጋቸው ነገሮች የመጻፍ እድል አግኝተናል።

በእግዚአብሔር ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለዉን ችላ የሚሉ ሰዎች በራሳቸው ትምክህት የታወሩ እና እግዚአብሔርንም እያጡ ነው። ጌታን በዕቅዱ መሠረት እየተከተሉት አይድለም። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ባልተቀላቀለ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ላይ አይገነቡም። በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ዓለት ላይ ሳይሆን በራሳቸው መሠረት ላይ ይገነባሉ።

የእግዚአብሔር ሰዎች ሆይ! በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን ቃል ፍጻሜ እንድታዩ ወደ **ጌታ እንዲህ ይላል** ተመለሱ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ወደ ተመሠረተው እውነተኛ እምነት ተመለሱ። የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጻዓት የሚያመለክቱ አስደናቂ ትንበያዎች በዓይናችን ፊት እየተፈጸሙበት ባለው ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው። በጨለማ ለተቀመጡት የቃሉን ብርሃን ያበራ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

ዮሐንስ በዮሐንስ 6:45 እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "በነቢያት ዘንድ ተጽፎአልና፡- ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ።" በተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል እንማራለን እናም አሁን ለዘመናት የተሰወሩትን የእግዚአብሔርን ምሥጢራት ማየት እንችላለን። በዮሐንስ 7:38 ላይ (ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር) እናነባለን፦ "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ

ወንዝ ከሆዱ ይፈስሳል::" ያኔ ብቻ የእግዚአብሔር በረከት በእኛ ላይ ሊያርፍ ይችላል።

እነዚህ "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ" የሚሉት ቃላት ከምንገምተዉ በላይ በጣም ጠቃሚ ናቸው። የምናደርገውና የምናምነው ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት መሆን አለበት። በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16-17 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፡- "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጻህፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለዉ ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡" ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ ቁመና ለመድረስ እና ወደ ፍጽምነት ለመቀጠል ከፈለግን፣ እንደ ዕብራውያን 6:1፣ በመንፈስ መሪነት የተጻፈዉን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ እና በእርሱ ውስጥ የተጻፉትን ተስፋዎች ሁሉ ማመን አለብን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ የደቀ መዛሙርቱን ለቃሉ መረዳት እንደከፈተ ማወቅ በጣም አሰፈላጊ ነው። በሉቃስ 24 ላይ፣ ከሁለት ደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ኤማሁስ መንገድ ሲሄድ እናነባለን። በእነዚያ ቀናት ስለተከናወነው ነገር ሁሉ ያወሩ ነበር፣ ነገር ግን ገና ግንዛቤ አልነበራቸውም፣ እናም ሁሉም ነገር ምን ማለት እንደሆነ አያውቁም ነበር። በዘመናችንም ብዙ ነገር ተከስቷል እና ሰዎች ስለእሱ እያወሩ ነው፣ ግን ኢየሱስን ስለማግኘትስ? እርሱ መረዳታችንን ከፍቶ ጥያቄያችንን ዛሬ ሊመልስ ይችላል። ደቀ መዛሙርቱ እንኳ ኢየሱስን "በኢየሩሳሌም እንግዳ ብቻ ነህን ወይስ በእነዚህ ቀናት የተደረገውን አላወቅህምን?" (ቁ. 18) አሉት። እርሱን አላወቁትም፤ ቅዱሳት መጻሕፍት መፈጸም እንዳለባቸውም አላስተዋሉም። ደቀ መዛሙርቱ እስከ ተናገሩ ድረስ፣ ግንዛቤያቸው ሊከፈት አልቻለም፣ ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ መናገር ሲጀምር፣ ያኔ የተከሰተውን ነገር በግልጽ ማየትና መረዳት ቻሉ። እውነተኛ ደቀ መዛሙርቶች ስለ እግዚአብሔር ነገሮች እያወሩ ፣ ሆኖም ግን ቅዱሳት መጻሕፍት እየተፈጸሙ መሆናቸውን ሳያዉቁ ይችላሉ ። ቁልፉ በሉቃስ 24:25 ላይ ባሉት የኢየሱስ ቃላት ውስጥ ነው፦ "እናንተ የማታስተውሉ፣ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ ! ክርስቶስ ይህን ሁሉ መከራ ይቀበል ዘንድ እና ወደ ክብሩም ይገባ ዘንድ ይገባዉ የለምን? አላቸዉ" ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሁሉም ነገር በነቢያት እንደተነገረው መፈጸም እንዳለበት እንዴት እንዳሳሰበ እናያለን።

ይህ በጣም አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ጊዜ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ያው ነው። በእውነት ደቀ መዛሙርቶቹ ከሆንን፣ የእርሱ ቃል ብርሃንንና ለዚህ ጊዜ የተነገሩ ትንቢቶች እንደተፈጸሙ ለመረዳት የሚያስችል ግንዛቤን ይሰጠናል። ብዙ ትንቢቶች በምንኖርበት ዘመን እየተፈጸሙ ነው። እነዚህ ትንቢቶች በመጀመሪያ ከቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ትኩረታችን መምጣት አለባቸው። የቅዱሳት መጻሕፍትን ትንቢቶች እንደፈለግን ማብራራት እንደማንችልም መረዳት አለብን። የእግዚአብሔርን ምሥጢራት ለመናገር

በእግዚአብሔር የተላከ ነቢይ ያስፈልጋል። ወንድም ብራንሃም እንዳለው፣ “እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው።” እርሱ የተናገረውን እንዲፈጸም በማድረግ የእራሱን ቃል ይተረጉመዋል።

ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት እግዚአብሔር የሚያደርገዉን ለመረዳት የሚፈልጉ ሁሉ ከክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት በፊት እግዚአብሔር የሠራውን መረዳት አለባቸው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ ቃሉ ወደ ነቢያት እንደመጣ በተደጋጋሚ እናነባለን። ነቢያት እግዚአብሔር የእርሱ ሕዝብ እንዲያውቁት የፈለገውን በራእይና በመገለጥ አይተዋል። በአሞጽ 3:7 ላይ የታወቀውን ቅዱስ ጽሑፍ እናነባለን፦ “ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ሳይገልጥ ምንም አያደርግም።”

የእግዚአብሔር ምስጢራት የሚገለጠዉ ለወንጌላዊ ወይም ለሰባኪ ነዉ አይልም፣ ነገር ግን ለባሪያዎቹ፣ ለእግዚአብሔር ነቢያት እንደሚገለጥ ነዉ። ጳውሎስ ይህን እውነታ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አጽንዖት ሰጥቶ በኤፌሶን 3:5 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “ ይህም ሚስጥር አሁን ለቅዱሳኑ ሐዋርያትና ነቢያት የተገለጠዉን ያህል ባለፉት ዘመናት ለነበሩ ሰዎች አልተገለጠም ነበር።” መለኮታዊውን ሥርዓት ማክበር እና እግዚአብሔር የሚያደርገውን በትክክል እንድንረዳ እንዲረዳን መጠየቅ አለብን።

እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ የራሱን ሀሳብ አይናገርም፣ የቤተ እምነትንም አመለካከት አያዉጅም፣ ይልቁንም በእግዚአብሔር በተሰጠ ሥልጣን በጌታ ስም ይናገራል። በዚህ ነጥብ ላይ በ2ኛ ዜና መዋዕል 20:20 ላይ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ቃል መግለጫ መጥቀስ አለብን፦- “ኢዮሣፍጥም ቆሞ እንዲህ አለ፦- ስሙኝ ይሁዳና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሆይ፤ በአምላካችሁ በጌታ እመኑ፤ትጸኑማላችሁ፤ በነቢያቱም እመኑ ይሳካላችሁማል።”

እነዚህ ቃላት በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት እንደተነገሩ በእርግጠኝነት እናምናለን። በቀላሉ ማለፍ የለብንም፣ ነገር ግን በጥቅሱ መጨረሻ ላይ የተነገረውን ማሰብ አለብን፦- “በአምላካችሁ በጌታ እመኑ ትጸኑማላችሁ፤ ነቢያቱንም እመኑ ይሳካላችሁማል።” በሐጌ 1:12-13 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፦- “ሊቀ ካህናቱ ከሕዝቡም የቀረው ሁሉ የአምላካቸውን የጌታን ቃል ነቢዩ ሐጌ የተናገረውን ቃል ሰሙ፤ አምላካቸውም ጌታ እንደ ላከው ሕዝቡ በጌታ ፊት ፈሩ። ከዚያም ነቢዩ ሐጌ የጌታን መልእክት ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ተናገረ፦ ከእናንተ ጋር ነኝ ይላል ጌታ።”

ይህ ቅዱስ ጽሑፍም በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቷል እና ለትምህርት ይጠቅማል። እዚህ ላይ የጌታን መልእክት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለሰጠው የጌታ መልእክተኛ እናነባለን። በዚህ ቅዱስ ጽሑፍ ውስጥ በጣም አስፈላጊው ነገር፣ የቀረው የሕዝቡ ክፍል የአምላካቸውን የጌታን ቃል፣ አምላካቸውም ጌታ

እንደ ላከው የነቢዩ ሐጌን ቃል መታዘዛቸው እና ሕዝቡ ጌታን መፍራታቸው ነው።

በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር ምን ቃል እንደገባ መረዳት አለብን፣ እናም እግዚአብሔር ነቢይ እንደላከ ስንገነዘብ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ፈቃደኛ መሆን አለብን። ከዚያም ጌታ ከእኛ ጋር ይሆናል፣ ስለዚህም እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ በጌታ ስም ከእግዚአብሔር ቃል የሚያደርሰውን መልእክቱን እና መልዕከተኛዉን መቀበል እንችላለን። ያለምንም ማመንታት፣ በዚህ ትውልድ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቅሬታ ሕዝብ የአምላካቸውን የጌታን ድምፅ እንደሚታዘዙ መናገር ይቻላል፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር የተላከውን የነቢዩን ቃል ያዳምጣሉ። መልእክተኛውን እና መልእክቱንም ተቀብለዋል። አስቀድሞ እንደተጠቀሰው፣ በብሉይ ኪዳን የጌታን የመጀመሪያ ምጽአት የሚመለከቱ ትንቢቶች ነበሩ። ከመፈጸማቸው በፊት፣ እግዚአብሔር ዮሐንስ የተባለ ነቢይ ላከ። እርሱ የጌታን መንገድ አዘጋጀ እና የተጻፈዉን ቃል ለመግለጥ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር የተነገረውን ቃል ለሕዝቡ አምጣ። በተነገረው ቃል አማካኝነት የተጻፈው ቃል ተገልጧል። የዮሐንስን መልእክት ያመነ ሁሉ፣ በእውነቱ፣ እግዚአብሔርን አመነ። አሁን እኛ የምንኖረው ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ነው እናም እንደገና ትንቢቶች እየተፈጸሙ ነው። የዚህን ሰዓት መልዕክት በእግዚአብሔር የተላከው ነቢይ ያደረሰውን መልእክት የሚያምን ሁሉ የቅዱሳት መጻሕፍትን ፍጻሜ ያያል።

የምናምነውንና የምናስተምረውን ነገር ፍጹም እርግጠኝነት ለማግኘት በዚህ ዘመን **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለው ያስፈልገናል። በዮሐንስ ዘመን ይሰብኩ የነበሩ ብዙዎች ከወቅቱ መልእክት ጋር በአንድ መስመር ዉስጥ አልገቡም እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል በዓይናቸው ፊት እየተፈጸመ እንደሆነ አላወቁም። ተመሳሳይ ነገር በዚህ ጊዜ ሊከሰት ይችላል። ቅዱሳት መጻሕፍት እየተፈጸሙ መሆናቸውን ሳንገነዘብም ስለ ጌታ መምጣት እንኳን ልንናገር እንችላለን ። ሆኖም ግን፣ እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ ችላ ብለን፣ እግዚአብሔር በዚህ ትውልድ የተነበየውንና የፈጸመውን ውድቅ ካደረግንና ካላስተዋልን፣ የእግዚአብሔርን ልጅ እንደገና እንሰቅለዋለን።

እግዚአብሔር የሚይሰራዉን ሥራ ማለፍ አይቻልም። የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጅ ከሆንክ፣ እውነተኛ መልእክተኛውንና የእግዚአብሔርን መልእክት ታዉቃለህ እና ትቀበላለህ ። እንደ ሐዋርያት ሥራ 1:16፣ ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ከመቶ ሃያዎቹ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ፡- “ ወንድሞች ሆይ ፤ ኢየሱስን ለያዙት መሪ ስለነበረው ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ በዳዊት አፍ አስቀድሞ የተናገረው የመጻሕፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ይገባ ነበር።”

በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት፣ ጴጥሮስ የቅዱሳት መጻሕፍትን መፈጸም በይሁዳ ላይ በደረሰው ነገር ውስጥም አይቷል። ይህን ምዕራፍ እስከ

መጨረሻው ማንበብ አለብን ምክንያቱም ጴጥሮስ መፈጸም ወደ ነበረባቸው ትንቢቶች ያለማቋረጥ ይጠቀሳል። ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ አገልጋይ ባሕርይ ነው። በደንብ የተዘጋጁ ማብራሪያዎችን አያመጣም ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** ይመልሳል።

በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ እናነባለን። በቁጥር 14 እንደገና ጴጥሮስ ነዉ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆሞ ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፡- "እናንተ የይሁዳ ሰዎች ሁሉ፣ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁሉ፣ ይህን እወቁ፣ ቃሌንም አድምጡ፤ ለእናንተ እንደመሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይድሉም ፤ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና። ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዮኤል የተባለዉ ነዉ ። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በመጨረሻው ዘመን እንዲህ ይሆናል መንፈሴን በሥጋ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፤ ጎበዛዝቶቻችሁም ራእይ ያያሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ።"

ጴጥሮስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ሥር፣ የትኛው ትንቢት እንደተፈጸመ በትክክል አዉቆ እንደነበር እናያለን። በብዓለ ኃምሳ ቀን ስለተከሰተው ነገር የራሱን ማብራሪያ አልሰጠም ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል ጠቀሰ። ነቢዩ ዮኤል ስለዚያ ተናግሮ እንደነበር ለሕዝቡ ማሳየት ችሏል።

በሐዋርያት ሥራ 3:18 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፦ "እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረዉን እንዲሁ ፈጸመዉ።" ይህ ድንቅ መግለጫ ነው። ክርስቶስን በመጥቀስ፣ በቁጥር 21 ላይ እንዲህ ይላል፦ "እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረዉ ፤ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ሰማይ ይቀበለዉ ዘንድ ይገባልና ።"

በዚህ ትንቢታዊ መግለጫ፣ ወደ ራሳችን ትክክለኛ ጭብጥ ደርሰናል። ክርስቶስ በሰማይ የሚጠብቀው ነገር ሁሉ እስኪመለስ ድረስ ፣እግዚአብሔር በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ እንደተናገረው በሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ መለኮታዊው ሥርዓት እንደገና እስኪገነባ ድረስ ነው ። ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ይህን ቃል ስለ ሁሉ ነገር መመለስ በተናገረበት ጊዜ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ከረጅም ጊዜ በፊት አልቋል።

ይህ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 17:11 ከተናገረው ጋር ይስማማል፣ እዚያም እንዲህ ሲል እናነባለን፡- "ኤልያስ በእውነት አስቀድሞ ይመጣል፤ ሁሉንም ነገር ይመልሳል።" ይህ የተነገረና የተጻፈው በወደፊት ጊዜ ነው። ይህ ሊካድ አይችልም። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን የተናገረው የዮሐንስ አገልግሎት ካለቀ በኋላ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ጌታቸውን እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፦ "ታዲያ ጸሐፍት ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣል ለምን ይላሉ?" መልሱ ኤልያስ እንደሚመጣ እና ሁሉንም ነገር እንደሚመልስ ነበር። ከዚያም ከዮሐንስ ጋር በተያያዘ እንዲህ አለ፦ "ኤልያስ መጥቶአል፤ እነርሱም አላወቁትም።" ኢየሱስ

ይህን የተናገረው ስለ ነቢዩ ኤልያስ መላክ የተነገረው ትንቢት የመጀመሪያ ክፍል ስለተፈጸመ ነው። "የአባቶችን ልብ ወደ ልጆቻቸው ይመልሳል..." (ሉቃስ 1:17)። እዚህ ላይ እንደ ሉቃስ 4:19 ያለ ምስጢር አለ፣ ኢየሱስ ስለ ጌታ ተቀባይነት ያለው ዓመት ያነበበበት ነገር ግን ስለ በቀል ቀን የተጻፈውን የተወበት።

ስለዚህ እግዚአብሔር ክክርስቶስ ከመጀመሪያው ምጽአት በፊት ነቢይ እንደሚልክ ፤እንዲሁም ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ነቢይ እንደሚልክ የሰጠውን ተስፋ እናያለን። ከጌታ ታላቅና አስፈሪ ቀን በፊት ነቢዩ ኤልያስን የመላክ ተስፋ በሚልክያስ 4:5 ላይ ይገኛል፦ "እነሆ፥ ታላቁና የሚያስፈራዉ የጌታ ቀን ሳይመጣ ነቢዩ ኤልያስን እልክላችኋለሁ!" የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ታላቁና አስፈሪው የጌታ ቀን ከመግባቱ በፊት መከሰት አለበት።

ጸሐፍት ኤልያስ እንዳደረገው በሕዝቡ መካከል ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቆችን የሚያደርግ ሰው እየጠበቁ እንደነበር ግልጽ ነው። ዮሐንስ የቃሉ ነቢይ ነበር፣ ሆኖም ግን በአገልግሎቱ ምንም ምልክትና ድንቅ አልተደረገም። እርሱ ከጌታ ታላቅና አስፈሪ ቀን በፊት የሚመጣው ያ ነቢይ ኤልያስ አልነበረም። የጌታ ቀን በዮሐንስ ዘመን ቅርብ አልነበረም፤ ይልቁንም የጸጋና የመዳን ቀን መጀመሪያ ነበር። እርሱ በቀላሉ በኤልያስ ኃይልና መንፈስ የቆመ ነቢይ ነበር። መልአኩ ዘካርያስን በሉቃስ 1:17 እንዲህ አለው፦ "በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል። የአባቶችን ልብም ወደ ልጆች ይመልሳል።"

እያንዳንዱን ቃል በትክክል ማንበብ በፍጹም አስፈላጊ ነው። ኤልያስ ነው አይልም፣ ነገር ግን በኤልያስ መንፈስና ኃይል እንደሚመጣ ብቻ ይናገራል። በዮሐንስ 1:19 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፦ "ይህም የዮሐንስ ምስክርነት ነው፤ አይሁድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ ፦ አንተ ማን ነህ? ብለው ጠየቁት። እርሱም መሰከረ አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ። እነርሱም፦ እንግዲያውስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? አሉት። እርሱም አይደለሁም አለ።"

ዮሐንስን ውሸታም ብለን መጥራት ካልፈለግን፣ የተናገረውን ማመን አለብን። በቁጥር 23 ላይ፣ ስለ እርሱ በተተነበየው የመጻህፍ ቅዱስ ጥቅስ መለሰ:- "እርሱም ፦ ነቢዩ ኢሳያስ እንዳለ ፦ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰዉ ድምጽ እኔ ነኝ አለ።"

የዮሐንስ ምስክርነት እና መልአኩ ለዘካርያስ የተናገረው ከኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማል። ስለ ዮሐንስ በማቴዎስ 11:10 ላይ እንዲህ ተጽፏል፦ " እነሆ ፤ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና።" በሚልክያስ 3:1 ላይ በትክክል ተጽፎ የምናገኘው ይህን ነው። ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ

የተናገረው ነው፣ እናም የተናገረውን ማመን አለብን። ዮሐንስ በእርግጠኝነት ከጌታ ታላቅና አስፈሪ ቀን በፊት የሚመጣ ነቢይ ሊሆን አይችልም። ሁለት ሺህ ዓመታት ያህል አልፈዋል፣ እናም የጌታ ታላቅና አስፈሪ ቀን ገና አልመጣም። እንደ እግዚአብሔር ቃል፣ በብሉይ ኪዳን የመጨረሻዎቹ ሁለት ቁጥሮች ላይ እንደምናነበው፣ በትንቢት ሚልክያስ ውስጥ፣ ኤልያስ ከጌታ ታላቅና አስፈሪ ቀን በፊት መምጣት አለበት። እርሱም የልጆችን ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል፣ ጌታ ምድርን በእርግማን እንዳይመታ።

አሁን የጌታ ቀን የተገለጸባቸውን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች እንጥቀስ። በ2ኛ ተሰሎንቄ 2:2 ላይ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ "የጌታ ቀን ቀርቧል ብላችሁ፣ በቶሎ በአእምሯችሁ እንዳትናወጡ ወይም እንዳትደናገጡ፣ በመንፈስ ቢሆን ወይም በቃል ቢሆን ወይም ከእኛ እንደሆነ በሚመስል ደብዳቤ ቢሆን።" በእርግጥ፣ የመጀመሪያው ምጻአት ቀዳሚን ከሁለተኛው ምጻአት ቀዳሚ ጋር ያቀላቀሉ ሰዎች ነበሩ ማለት ነዉ። ይህ ደግሞ ዛሬም እየሆነ ነው፣ ያለበለዚያ ጳውሎስ በዚህ የጌታ ቀንን በሚመለከት ርዕሰ ጉዳይ ላይ መጻፍ ባላስፈለገው ነበር። ጳውሎስ ሐዋርያና ነቢይ ነበር። ስለ ክህደት እና የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ስለሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ ገለጸ። በመሠረቱ፣ ጳውሎስ የሚለው የጌታ ቀን ሊመጣ የሚችለው በ2ኛ ተሰሎንቄ 2 እና በሌሎች የመጨረሻዉ ዘመንን በተመለከተ የተጻፉት ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ ብቻ ነው።

የጌታ ቀን በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ተገልጿል። ለምሳሌ፣ ኢሳይያስ 13:6+9 እንዲህ ሲል እናነባለን፦ "የጌታ ቀን ቀርቧልአልና፤አልቅሱ ፤ ሁሉን ከሚችል አምላክ ዘንድ እንደሚመጣ ጥፋት ይመጣል። እነሆ፤ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ፤ኃጢአተኞችዋንም ከእርስዋ ዘንድ ሊያጠፋ ጨካኝ ሆኖ በመዓትና በጽኑ ቁጣ ተሞልቶ የጌታ ቀን ይመጣል ።"

በነቢዩ ሶፎንያስ 1:14-15 ላይ እንዲህ ሲል እናነባለን፦ "ታላቁ የጌታ ቀን ቀርቦአል፤የጌታ ቀን ድምጽ ቀርቧል እጅግም ይቸኩላል። ኃይሉም በዚያ በመራራ ልቅሶ ይጮኻል። ያ ቀን የመዓት ቀን የመከራና የጭንቀት ቀን ፤ የመፍረስና የመጥፋት ቀን ፤ የጨለማና የጭጋግ ቀን፤ የጨለማ እና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ነዉ ።"

በኢዮኤል 2:31 ላይ ማንበብ እንቀጥላለን፦ "ታላቁና አስፈሪው የጌታ ቀን ከመምጣቱ በፊት ፀሐይ ወደ ጨለማ፣ ጨረቃም ወደ ደም ትለወጣለች።"

ይህ በዩኤል 2፡31 የተጠቀሰዉ ቅዱስ ጽሑፍ ስድስተኛውን ማኅተም ያስታውሰናል። ስድስተኛው ማኅተም ምን እንደያዘ ለማወቅ ሁሉም ራዕይ ምዕራፍ ስድትን፣ ከቁጥር አስራ ሁለት ጀምሮ ማንበብ ይችላል።

ወዲያዉኑ መነጠቅ እንደተከሰተ ለአህዛብ የጸጋና የመዳን ቀናት ይጠናቀቃሉ ። ከዚያም የቁጣና የበቀል ቀን ይጀምራል። ጴጥሮስ በ2ኛ ጴጥሮስ

3:10 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “ነገር ግን የጌታ ቀን ሌባ እንደሚመጣ ይመጣል፤ በዚያም ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ የሰማይም ፍጥረታት በብርቱ እሳት ይቀልጣሉ፤ ምድርም በእርሷ ያሉት ሥራዎችም ይቃጠላሉ።”

ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5:2 ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “የጌታ ቀን ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፤እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ በትክክል ታውቃላችሁና።” በተጨማሪም በአራተኛው ቁጥር ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “እናንተ ግን ፤ ወንድሞች ሆይ ፤ ቀኑ እንደሌባ ይደርስባችሁ ዘንድ በጨለማ አይድላችሁም።”

ይህ ትንቢትም ተፈጽሟል። ጳውሎስ እኛ ልንሸነፍ እንደማንችል ይጽፋል፣ ምክንያቱም በጨለማ ውስጥ አንኖርምና። ነቢዩ ዘካርያስ በምዕራፍ 14:7 ላይ እንዲህ ሲል ተንብዮአል፦ “ነገር ግን በጌታ ዘንድ የሚታወቅ አንድ ቀን ይሆናል፤ ቀንም አይሆንም፣ ሌሊትም አይሆንም፤ ነገር ግን ምሽት ላይ ብርሃን ይሆናል።” በዚህ ዘመን በተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን የሚኖሩት ከእንግዲህ በጨለማ ውስጥ አይደሉም። በእግዚአብሔር የተመረጡት በዚህ ትውልድ እርሱ የእራሱን አገልጋይና ነቢይ ከጌታ ታላቅና አስፈሪ ቀን በፊት እንደላከ ተገንዝበዋል።

እዚህ ላይ በዚህ ጊዜ ወንጌልን ለሚያገለግሉ አገልጋዮች ሁሉ ጥቂት ጥያቄዎች አሉኝ፣ እነርሱም ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ጉብኝት ያላወቁትን እና የትንቢትን ፍጻሜ ያላዩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ሰዎችን ይከሱ ነበር። ሳንገነዘብ እኛም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ልንገኝ አንችልም ወይ? እግዚአብሔር በዘመናችን እያደረገ ያለውን ነገር ችላ ብለን እያለፍን አይድለም ወይ? የራሳችንን ፕሮግራሞች ብቻ ስለምናይ እና የእግዚአብሔርን ዕቅድ ስለማንገነዘብና ጌታ በነቢያቱ አፍ የተናገረውን የቃሉን ፍጻሜ ስለማናይ የእግዚአብሔርን ሥራ መረዳት ተስኖን ይሆን?

የእግዚአብሔርን ዘላለማዊና የማይጠፋ ቃል መንገዳችንን ለማብራት መውሰድ በፍጹም አስፈላጊ ነው። የጌታችንን ድንቅ ቃላት በዮሐንስ 8:12 ላይ እናነባለን፦ “ኢየሱስም ደግሞ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፦ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይኖረዋል እንጅ ፤ በጨለማ አይመላለስም።” ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ነው። እርሱን ለመከተል፣ የዚህን ሰዓት ቃል መከተል አለብህ። ስንት ሰዎች በአፋቸው “ቃልህ ለእግሬ መብራት፤ ለመንገዴም ብርሃን ነውና” (መዝ. 119:105) ይላሉ፣ ነገር ግን አሁንም በጨለማ ውስጥ መሄዳቸውን ቀጥለዋል። የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ መግለጥ በመለኮታዊ ትርጉሙ ካልተገለጠልን በቀር ደማቅ የሚያበራ ብርሃን ሊሆን አይችልም። ወንድም ብራንሃም ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፦ “ሰዎች እግዚአብሔር ላደረገውና ለሚያደርገው ነገር እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ ነገር ግን በዘመናቸው እያደረገ ያለውን ያጡታል እና ያልፋቸዋል።”

አሁን ምርጫ አለን። የራሳችንን ትርጓሜዎች ማመንንና መስበካችንን መቀጠል ፣ ወይም ደግሞ በዚህ ዘመን በወንድም ብራንሃም ትንቢታዊ አገልግሎት የተላከውን የእግዚአብሔርን ቃል መቀበል እንችላለን። አብዛኛው ሰው እግዚአብሔር ለዚህ ዘመን ቃል የገባውን አያውቅም። እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ አገልጋዮቹን ነቢያትን ተጠቅሞ የሚሆነውን ነገር እንደገለጠ መማርና መቀበል አለብን። በምድር ላይ ያልተለመደ ነገር ሊከሰት በነበረበት ጊዜ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ሊናገርበት የሚችል ነቢይ ሁልጊዜ ዝግጁ ያደርግ ነበር። ሁሉም ሰባኪና ወንጌላዊ ትንቢታዊ አገልግሎት እንደሌለው መረዳት አለብን። ነቢይ ብቻ ነው ትንቢታዊውን ቃል ለሕዝቡ መግለጥ የሚችለው። እግዚአብሔር ነቢያትን ነገሮችን አስቀድሞ ለመናገር እንደተጠቀመባቸው ሁሉ፣ ሲፈጸሙም በፍጻሜው ጊዜ ለማወጅ ነቢያትን ይጠቀማል። እግዚአብሔር ቃሉን ለመፈጸም ስለሚጠብቀው እርሱ የተመሰገነ ይሁን።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ 17:26-30 ላይ እንዲህ ሲል ተንብዮአል፦ “በኖኅ ዘመን እንደ ሆነ፤ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ይበሉና ይጠጡም ያገቡና ይጋቡም ነበር፣ ከዚያም የጥፋት ውኃ መጣ ሁሉንም አጠፋቸው። እንዲሁ ደግሞ በሎጥ ዘመን እንደ ሆነ፤ ይበሉም ይጠጡም ይገዙም ይሸጡም ይተክሉም ቤትም ይሠሩ ነበር፣ ነገር ግን ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ዕለት ከሰማይ እሳትና ዲን ዘነበ ሁሉንም አጠፋቸው። የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል።”

እግዚአብሔር ያን ጊዜ ያደረገውን በማሰብ አሁን ምን እያደረገ እንዳለ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። አብዛኞቹ አማኞች የሚያወሩት በዚያን ዘመን በማያምኑት መካከል ስለተከሰቱት ነገሮች ብቻ ነው። ነገር ግን እኛ የእግዚአብሔር ልጆች፣ የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ እየጠበቅን፣ በዋነኛነት የምንፈልገው በዚያን ጊዜ በተጠሩት መካከል ምን እንደተከሰተ ለማወቅ ነው። የጥፋት ውኃው ፍርድ ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ነቢይ እንደነበረው እውነት ነው። እርሱም የፈቃዱን ምስጢር ለዚያ ነቢይ ገለጸለት እና እርሱን ያመኑ ሁሉ አመለጡ እና ደህና ሆኑ።

በዚያን ጊዜ ከእግዚአብሔር የተባረኩ የሴት ዘሮች ነበሩ፣ እንዲሁም የቃየል ዘር ነበሩ። እነዚህ ሁለቱ ሲቀላቀሉ፣ የሥጋ ሁሉ መጨረሻ በእግዚአብሔር ፊት መጣ። ክርስቶስ በስጋ የዘር ሐረጉ ከቃየል ጋር ካልተቀላቀለ ከሴት ዘር ነዉ መወለድ የነበረበት። በዚህ ትውልድ፣ የሃይማኖት ዓለም እየተሰበሰበ እና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ውስጥ እየተቀላቀለ ነው። ልክ እንደዚህ ባለ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ልጆች እንዲጠራ መልእክት አሰይዞ ነቢይ ልኳል፣ እነርሱም እውነትን ለማመን ተለይተው እንዲወጡ። የእግዚአብሔርን ቃል እውነት የማይቀበሉና የማያምኑ ሁሉ የሰይጣንን ውሸት ማመን አለባቸው። ስለ እግዚአብሔር ነቢይ ኖኅ ሲያወሩ ሰዎች እንዴት ይሳለቁና ራሳቸውን ይነቀንቁ እንደነበር መገመት እንችላለን።

ነገር ግን እግዚአብሔር በስሙ የተነገረውን የሚያረጋግጥበት ጊዜ መጣ። በዚህ ትውልድም እንዲሁ ይሆናል።

እግዚአብሔር በዚያ ዘመን ነቢይ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ አሁንም ነቢይ ሊኖረው ይገባል፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሉቃስ 17:30 ላይ እንዲህ አለ ፦ “የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል።” ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቅ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ ለዚያ ዘመን የተገለጠለት ሰው ኖኅ ብቻ ሊሆን አይችልም ብለዉ አስበው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን ኖኅ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኑ የተረጋጠ እዉነታ ነበር።

ወዳጆች፣ ቅዱስ ጽሑፍ ሊፈርስ አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ በማቴዎስ 24:37-39 ላይ እንዲህ አለ፦ “በኖኅ ዘመን እንደ ሆነወ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።በዚያች ወራት ከጥፋት ዉኃ በፊት ፤ኖኅ ወደ መርከብ አስከገባበት ቀን ድረስ፤ ሲበሉ እና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደነበሩ፤ የጥፋት ዉኃም መጥቶ ሁሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፤የሰዉ ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።”

ትንቢት በዓይናችን ፊት እየተፈጸመ ነው ብለን በእውነት መናገር እንችላለን። የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ከመውደቁና የሰዶምና የገሞራ ከተሞች ከመቃጠላቸው በፊት የተከናወኑትን ክስተቶች እንመልከት። እንደ ዘፍጥረት 18፣ ጌታ የእርሱ ነብይ የሆነዉን አብርሃምን ከሁለት መላእክት ጋር ጎበኘው። በዘፍጥረት 19:1 ላይ፣ ሁለቱ መላእክት ወደ ሰዶም ሲሄዱ እናነባለን፣ ነገር ግን ጌታ ከአብርሃም ጋር ቀረና አለው፦ “ እኔ የማደርገዉን ከአብርሃም እሰዉራለሁን?” (ዘፍ. 18:17)።

አብርሃም በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር እናም የእግዚአብሔር ፈቃድ ምስጢራት ለእርሱ ተገለጡለት። እባክችሁ ዘፍጥረት 18:9-15ን በጥንቃቄ አንብቡ። ጌታ ሣራ በድንኳን ውስጥ ሆና ንግግሩን እየሰማች ሳለ ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ አረጋገጠ። እርስዋ በውስጧ ሳቀች። ከዚያም ጌታ፣ ለአብርሃም ሲናገር እንደሳቀች ገለጠለት። የእርሷን የልብ ሀሳብም አስታወቀ (ቁ. 13)። ይህን ክስተት በደንብ መረዳት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍርድ በሰዶምና በገሞራ ከመውደቁ በፊት የተከሰተው የመጨረሻው ነገር ነበር።

በዚያን ዘመን የተከሰተውን ካልተረዳን፣ በእርግጠኝነት አሁን እየሆነ ያለውን ነገር መረዳት አንችልም። ጌታ በዚህ ምድር ሲመላለስ የነበረዉ አገልግሎት ሰዶምና ገሞራ ከመጥፋታቸው በፊት ከአብርሃም ጋር ከነበረዉ ጋር ያለዉን ተመሳሳይነት ለማየት ችለናል? ጌታ ራሱን ለአብርሃም አስታውቋል። በመጀመሪያ ምጽአቱም ራሱን ለአብርሃም የንጉሣዊ ዘር አስታውቋል። አብርሃም

እግዚአብሔርን እንዳመነ ሁሉ፣ ጌታ በዚህ ምድር ላይ እራሱን ገልጦ ሲመላለስ የአብርሃም ዘርም እግዚአብሔርን አምኗል።

በዮሐንስ ወንጌል፣ ምዕራፍ 1:40-42 ላይ፣ እንድርያስ ወንድሙን ወደ ክርስቶስ እንዳመጣ ተዘግቧል። ጌታም ወደ እርሱ ተመልክቶ እንዲህ አለ፦ “አንተ ስምዖን የዮና ልጅ ነህ።” ከዚህ በፊት አግኝቶት አያውቅም፣ አሁን ግን በስሙ ጠራው አልፎ ተርፎም የአባቱን ስም ነገረው። እባካችሁ ይህን በቀላል አትለፉት ምክንያቱም ጌታ ያደረገው ነገር ሁሉ በእርግጠኝነት ታላቅ ትርጉም አለው። በዚሁ ምዕራፍ ላይ ፊልጶስ ናትናኤልን ወደ ክርስቶስ እንዳመጣ ተዘግቧል። ኢየሱስም እንዲህ አለ፦ “እነሆ ፤ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ የእስራኤል ሰው!” ናትናኤል በጣም ስለተደነቀ፣ በአግራሞት እንዲህ ሲል ጠየቀ፡ - “ከወዴት ታውቀኛለህ?” (ዮሐንስ 1:48) ከዚያም የጌታ መልስ መጣ፦ “ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ በታች ሳለህ አየሁህ።” ያ ለናትናኤል በቂ ነበር፣ እናም ጮኸ፦ “ረቢ፥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ” (ቁ. 49)። በዮሐንስ ወንጌል፣ ምዕራፍ 4፣ የሳምራዊቷን ሴት ታሪክ እናነባለን። ጌታ ኢየሱስ ሕይወቷን ገለጠላት። እርሷም እንዲህ አለችው፦ “ጌታ ሆይ ነቢይ እንደሆንህ አያለሁ።” ከዚያም እንዲህ አለች፦ “መሲሕ ክርስቶስ የሚባለው እንደሚመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ በመጣ ጊዜ ሁሉን ይነግረናል።” ኢየሱስም እንዲህ አላት፦“የምናገርሽ እኔ አርሱ ነኝ” (ቁ. 25)። ያ ለሴቲቱ በቂ ነበር። እርሷም ተረድታ ወደ ከተማው ሮጠችና እንዲህ አለች፦ “ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰዉ ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን?” (ቁ. 29)።

በዚህ ጊዜ የወንድም ብራንሃምን አገልግሎት በትክክል ለመረዳት የሚፈልግ ሰው፣ በመጀመሪያ የጌታን አገልግሎት መረዳት አለበት። በወንድም ብራንሃም ስብሰባዎች ላይ የነበሩ ሰዎች፣ ያው ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተመሳሳይ መንገድ ራሱን እንደገለጠ መካድ አይችሉም። በመቶዎች የሚቆጠሩ የተቀረጹ መልዕክቶች ለዚህ እውነታ ሕያው ምስክር ናቸው። እንዲሁም፣ በዚህ ዘመን፣ የእግዚአብሔር እዉነተኛ ዘር የክብር ጌታ ስላደረገዉ ነገር እዉቅና ሰጥቷል ደስም እያለው ነው። የእባቡ ዘር የጌታ ሥራ ከዲያብሎስ እንደሆነ አወጀ። ያኔ እንደነበረው፣ አሁንም እንደዚያው ነው። ነገር ግን ጌታ በተአምራዊ ሁኔታ ራሱን ለገለጠለት እያንዳንዱ ሰው፣ የእግዚአብሔር እንደሆነ እርግጠኛ ነበር።

አራቱን ወንጌሎች የሚያነብ ማንኛውም ሰው፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎች የሚያስቡትን እና ያደረጉትን መንገር እንደሚችል ያገኛል። ለምሳሌ፣ በዮሐንስ 2:24-25 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ “ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፣ ስለ ሰዉም ማን ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመንባቸዉም ነበር፤ራሱ በሰዉ ያለዉን ያዉቅ ነበርና።”

በማቴዎስ 21:1 መሠረት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ደቀ መዛሙርትን ልኮ እንዲህ አላቸው፡- "በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፣ ወዲያውም የታሰረች አህያና ውርንጫዋን ከእርሷ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ። ማንም አንዳች ቢላችሁ፣ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ እርሱም ወዲያው ይልካቸዋል።ለጽዮን ልጅ ንገሯት፡- እነሆ፣ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ተቀምጦ ወደ አንች ይመጣል በሉአት ተብሎ በነብይ የተነገረዉ ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ።" በእርግጥም ደቀ መዛሙርቱ ጌታ እንደነገራቸው ሁሉንም ነገር እንዳለ አገኙት።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሰው በልቡ የሚያስበውን ያውቅ ነበር፣ እናም እርሱ እንደተናገረው በትክክል ስለሚሆኑ ነገሮች መናገር ይችላል። እውነተኛው የእግዚአብሔር ዘር በዚህ የጌታ ተአምራዊ አገልግሎት አልተሰናከለም፣ ይልቁንም የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን አምኖ ነበር። ስለዚህም ተባረኩ። ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ እንደ ሰው ልጅ ሲመላለስ፣ የነቢይነትን ሥራ ሲያከናውን፣ የአገልግሎቱን ባሕርይ ማየት እንችላለን። አንዳንዶች የተሰናከሉበት የመንፈስን መለየት ተአምራዊ አገልግሎት ነበር፣ ነገር ግን መንፈሶች የተለዩበትና የወጡበት በዚህ ዓይነት አገልግሎት ነበር። በእንደዚህ ዓይነት አገልግሎት ፊት ገለልተኛ ሆኖ መቆየት አይቻልም ነበር። የእግዚአብሔር ዘር የእግዚአብሔር ነው ሲል፣ የእባቡ ዘር ግን የዲያብሎስ ነው ብሎ አወጀ። የጊዜ መጋረጃው ተነስቶ፣ በእውነት የሚያምኑ የአብርሃምን ዘር የመጨረሻ መዳረሻ ማየት ብንችል ብለን እንመኛለን። በተመሳሳይ፣ የጌታን ሥራ የናቁትና በእርሱ ላይ ኃጢአት የሠሩትንም ማየት ብንችል፣ ይህ ከባድ ማስጠንቀቂያ ይሆናል። እውነተኛው የአብርሃም ዘር በጌታ በኢየሱስ ዘመን አብርሃም የነበረውን ያንኑ አይነት እምነት እንደነበረው በድጋሚ መናገር አለብን። በተመሳሳይ፣ በዚህ ትውልድ ያለው እውነተኛው የአብርሃም ዘር አብርሃም እግዚአብሔርን እንዳመነ ሁሉ ያምናሉ ።

እግዚአብሔር በዘመናችን ያደረገውን ነገር በድብቅ አላደረገዉም፣ ይልቁንም በተቃራኒው፡ እግዚአብሔር ያደረገውን በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ምስክር ሆነዋል። የወንድም ብራንሃም መንፈስን የመለየት ስጦታ ያለው ትንቢታዊ አገልግሎት **የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ** ተአምራዊ አገልግሎት ነበር። እርሱም በዚህ ትውልድ ውስጥ በተመሳሳይ መንገድ ራሱን ገልጧል። ብዙውን ጊዜ፣ የልብ ምስጢሮች ከጌታ ምክር ለሚፈልጉ እንዲሁም በትምህርታዊ አገልግሎቱ ለሚጠራጠሩ ይገለጡ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቅ እና የኢየሱስ ክርስቶስን አገልግሎት የተረዳ ማንኛውም ሰው፣ በዚህ ትውልድ ተመሳሳይ አገልግሎት እንደተገለጠ ለመለየት አይሳነውም። እኛ ልንለው የምንችለው ነገር ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ በዓይናችን ፊት መፈጸሙን ነው።

ከመጀመሪያው የጌታ መምጣት በፊት፣ ሰዎች ትንቢቶች ሲፈጸሙ ለማየት አራት ሺህ ዓመታት ያህል ይጠባበቁ ነበር፣ ከዚያም፣ ሁሉም ማለት

ይቻላል በአንድ ትውልድ ውስጥ ተፈጽመዋል። የጌታን መመለስ ሁለት ሺህ ዓመታት ያህል እየጠበቅን ነው እናም በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች ኢየሱስ ክርስቶስ በእነርሱ የሕይወት ዘመን ወቅት እንደሚመለስ አስበው ነበር። በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ከክርስቶስ ሁለተኛ ምጽአት ጋር የተያያዙ ሁሉም ትንቢቶች የሚፈጸሙበት ትውልድ ውስጥ እየኖርን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 24:34 ላይ፣ ስለ እስራኤል ሕዝብ በተነገረው የበለስ ዛፍ ምሳሌ ላይ እንዲህ ብሏል፡- “እውነት እላችኋለሁ፣ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትዉልድ አያልፍም።” እስራኤል ሕዝብ ሆና እንደገና የቆመችበትን ሚያየው ያው ትውልድ፣ ከጌታ ሁለተኛ ምጽአት ጋር የተያያዙ የሁሉም ትንቢቶች ፍጻሜም ምስክር ይሆናል።

ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት በነበረው የክርስትና ዘመን፣ እንዲሁም በዚህ ዘመናችን ውስጥ አንዳንድ ልዩ ነገሮች አሉ። በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ የአይሁድ እምነት ግርማ ሞገስ ወርዷል። እስራኤል በሮማውያን ወረራ ሥር ትሠቃይ ነበር፣ በመጨረሻም በ70 ዓ.ም. ቤተ መቅደሱ ሙሉ በሙሉ ወድሞ የእስራኤል ሕዝብ በመላው ዓለም ተበተነ። ተመሳሳይ ነገር በዚህ ዘመን እየሆነ ነው፣ ነገር ግን አዝማሚያው ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ እየፈሰሰ ነው። እስራኤል ከመላው ዓለም እየተሰበሰበች ነው፣ ቤተ መቅደሱን እንደገና ለመገንባትም ዕቅዶች አሉ። የእስራኤል አሁን ያለው አቋም፣ ስለ እስራኤልና ስለአሕዛብ ዘመን ፍጻሜ የተነገሩ ብዙ ትንቢቶች በዚህ ትውልድ ውስጥ እንደተፈጸሙና እየተፈጸሙ መሆናቸውን ይነግረናል። አይሁዶች ከየአገሩ ሁሉ እየወጡ ወደ አባቶቻቸው ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደተመለሱ ሁሉ፣ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆችም በዚህ ሰዓት በእግዚአብሔር ተስፋ ለመቆም ከሁሉም ቤተእምነቶች እየወጡ ነው።

በየዘመኑ ሁሉ ጌታ ፈቃዱን በቃሉ አማካኝነት ገልጧል፣ ይህም ወደ ነቢያቱ ይመጣ ነበር። አሁን በሰው ልጅ ታሪክ ሁሉ ውስጥ በጣም አስገራሚ በሆነው ዘመን ውስጥ እየኖርን ነው። የአሕዛብ ዘመን ፍጻሜ ላይ ደርሰናል ማለት ይቻላል፣ እናም እግዚአብሔር ለዚህ ቀን ምን ቃል እንደገባ ማወቅ አለብን። ነቢዩ ዳንኤል በዳንኤል 12:4 ላይ እንዲህ ሲል መዝግቧል፡- “ዳንኤል ሆይ፣ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ፣ መጽሐፉንም አትም፣ ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ ፤እዉቀትም ይበዛል።” በተመሳሳይ ምዕራፍ በ9ኛው ቁጥር እንዲህ እናነባለን፡- “እርሱም እንዲህ አለኝ ፡- ዳንኤል ሆይ፤ ቃሉ እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ነዉና ሂድ።”

ብዙዎች እግዚአብሔር ምስጢራቱን ባለፉት ዘመናት ያልገለጠው ለምንድነው ብለው በቅንነት ጠይቀዋል። ገና አሁን ስለዚያ አንብበናል፤ እስከ መጨረሻው ዘመን ድረስ ሊጠበቁ የሚገባቸው ነገሮች እንደነበሩ። በራእይ 10:7 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ነገር ግን ሰባተኛው መልአክ መለከቱን በሚነፋባቸዉ

ቀናት ፤ ለአገልጋዮቹ ለነቢያት በገለጠላቸዉ መሰረት፣ የእግዚአብሔር ምስጢር ይፈጸማል።"

ራእይ 10:5ን እና ዳንኤል 12:5ን ስናነብ፣ አንድ ቃል ከሌላው ጋር እንዴት እንደሚገጣጠም እናያለን። በፍጻሜዉ ዘመን የሚፈጸሙትን ነገሮች እንዲጽፍ መልአኩ ገብርኤል ወደ ነቢዩ ዳንኤል እንደመጣ ማወቁ በጣም አስፈላጊ ሊሆን ይገባል ። በተመሳሳይ መልኩ መልአኩ በጳጥሞስ ደሴት ላይ ወደ ዮሐንስ መጣ። ወደ ዚህ ዘመን የእግዚአብሔር ነቢይ አንድ መልአክ እንደመጣ መስማት እና መረዳት ሊያስደንቀን አይገባም። በዳንኤል 8:17 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "እርሱም እኔ ወደቆምሁበት ስፍራ እየቀረበ ሲመጣ፤ ደንግጬ በግንባሬ ተደፋሁ ፤ እርሱም "የሰዉ ልጅ ሆይ፤ራእዮ ስለ ዘመኑ ፍጻሜ እንደሆነ አስተዉል" አለኝ"

ቀደም ሲል እንደተባለው፣ እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ሁሉ እና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚሆነው ሁሉ ትልቅ ትርጉም አለው። በዳንኤል 8:19 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "እርሱም እንዲህ አለኝ ፦ "ራእዩ በመጨረሻዉ ዘመን ሊሆን ያለዉን የሚመለክት ስለሆነ በኋላ በቁጣዉ ዘመን ምን እንደሚሆን እነግርሃለሁ" አለኝ።" ትንቢታዊው ቃል ስለ መጨረሻው ዘመን እና እስከመጨረሻዉ ቀን ተጠብቀዉ እንዲቀመጡ ስለተወሰኑ ነገሮች እንደሚናገር ማየት እንችላለን። ዮሐንስ በጳጥሞስ ደሴት በነበረበት ጊዜ፣ ከመጨረሻው ዘመን ጋር የተያያዙ ነገሮች ታይተውታል። በራእይ 1:1 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ቶሎ ይሆን ዘንድ ያለውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው የመገለጥ ራእይ፤ እርሱም በመልአኩ ለአገልጋዩ ለዮሐንስ ልኮ ገለጠው።" ተመሳሳይ ቃላት በራእይ 22:6 ላይም ይገኛሉ።

እንደ ወንድም ብራንሃም ምስክርነት፤ እ.ኤ.አ በግንቦት 7 ቀን 1946 ዓ.ም የጌታ መልአክም ወደ እርሱ መጣ። እግዚአብሔር እንዲያዉቅ ስለሚፈልጋቸዉ ነገሮች እንዲነግረዉ ከእግዚአብሔር ፊት ተልኮ ነበር። አንድ መልአክ ወደ ዳንኤልና ወደ ዮሐንስ እንደመጣ ማመን ከቻልን፣ አንድ መልአክ ወደ ወንድም ብራንሃምም እንደመጣ ለማመን በእርግጥ አይከብደንም። በእርግጥ፣ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ መልአኮች የእግዚአብሔርን መልእክት ለማምጣት በተደጋጋሚ እንደተላኩ እናነባለን። እኛ አሁን በመጨረሻው ዘመን መጨረሻ ላይ እንደምንኖር፣ እና የኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ እጅግ በጣም እንደቀረበ በእግዚአብሔር ፊት በሙሉ ልባችን አረጋግጠናል። ሙሽራይቱ ከመነጠቋ በፊት መዘጋጀትና መጠራት እንዳለባት እናውቃለን። በዚህ በመጨረሻዉ ዘመን የመልእክተኛው ነቢይ የመምጣት ዓላማም ይህ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽራ በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ከዚህ ሃይማኖታዊ ባቢሎን መውጣት አለባት። እኛም መለየት ፤መቀደስ እና ሙሽራውን ለመገናኘት ዝግጁ መሆን አለብን። ሙሽራዉ ቃል እንደሆነ

ሁሉ፣ ሙሽራይቱም የዚያ ቃል አካል መሆን አለባት:: በዳንኤል 12:10 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ “ብዙ ሰዎች ሰዉነታቸዉን ያጠራሉ ያነጡማል፣ ይነጥሩማል፣ ክፉዎች ግን ክፉትን ያደርጋሉ፤ክፉዎችም ሁሉ አያስተዉሉም፤ ጥበበኞች ግን ያስተዉላሉ::”

እግዚአብሔር ለእኛ እንድንሰማው የወሰነውን ቃል አሁን መስማት እንዳለብን አረጋግጠናል:: የድርጅቶችን አመለካከት ሳይሆን፣ ለዚህ ዘመን አዲስ ምግብ ሆኖ ሊሰጥ የሚገባውን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃል የምናውጅበት ጊዜ አሁን ነዉ:: **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለውን ከተቀበልን በኋላ፣ ሰው ሠራሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ከእንግዲህ አያስፈልጉንም:: አንድ ሰዉ የተስፋዉን ቃል የማያዉቅ ከሆነ ፣ ያ ሰው ሳያውቅ ቅዱሳት መጻህፍት እየተፈጸሙ ሊሆን ይችላል::

ጌታ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጣ ጊዜ፣ ሰዎች የተጻፈዉ የእግዚአብሔር ቃል ነበራቸውና መሲሑን ይጠባበቁ ነበር:: ሆኖም፣ ትንቢቶች በዓይናቸው ፊት ሲፈጸሙ ለማየት የመንፈስ ቅዱስ መግለጥ አልነበራቸውም:: ከመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ውጪ ለነበሩት፤ ሁሉም ነገር መልካም ይመስል ነበር:: የቤተ መቅደስ አምልኮ ነበራቸው፣ እና የየሁሉም ስብከትና መሥዋዕት ጭብጥ መሲሑን በተለያየ መንገድ ያመለክቱ ነበር:: ወደ ራሱ በመጣ ጊዜ፣ የራሱ የሆኑት አልተቀበሉትም:: አሁን በየቦታው፣ የእግዚአብሔር ልጆች የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ እየጠበቁ ነው:: አገልጋዮች ስለእርሱ ይሰብካሉ፣ ነገር ግን የዚህን ሰዓት መልእክት ስለማይገነዘቡ ለመርዳት እንቅፋት ሆነዋል::

በእግዚአብሔር በተላከ ነቢይ ብቻ የእግዚአብሔርን ቃል መለኮታዊ ትርጉም ማወቅ እንችላለን:: ቃሉ በነቢይ አገልግሎት ከተገለጠ በኋላ፣ የእግዚአብሔር ልጆች በጌታ ቃል ላይ እንዲመሰረቱ አስተማሪ ነገሮችን ለቤተ ክርስቲያን ማስረዳት ይችላል::

ዮሐንስ ለዘመኑ መልእክት ይዞ በእግዚአብሔር የተላከ ሰው ነበር:: በዮሐንስ 1:7 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ “ ሰዎች ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ፣ ስለ ብርሃን ለመመስከር መጣ::” በእርሱ በኩል ሁሉም ሰው ማመን አለበት የሚለው በጣም ትልቅ መግለጫ ነው:: የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት የተመረጠ ቡድን አልነበረም፤ የጌታን መንገድ ለማዘጋጀት የተላከው ይህ አንድ ሰው ነበር:: እግዚአብሔር ምስጢራቱን ለጸሐፍትና ለፈሪሳውያን አደራ አልሰጠም፣ ይልቁንም ለዚያ ለተወሰነ ዓላማ አስቀድሞ ለሾመው ለአንዱ ሰው ሰጠው:: የተጻፈዉ ቃል ብቻ መኖሩ በቂ እንዳልሆነ ማየት እንችላለን፣ ነገር ግን የተጻፈውን ቃል ለመግለጥ የተነገረዉን ቃል የሚያመጣ የእግዚአብሔር ሰው መምጣት ነበረበት::

ተመሳሳይ ነገር በዚህ ትውልድም እየሆነ ነው። እያንዳንዱ አገልጋይ እና የእግዚአብሔር ልጆች የተጻፈዉ ቃል አላቸው። ነገር ግን እኛ እንድናውቅ የተወሰኑትን ምስጢሮች የሚያወጅ ቀድሞ የተሾመ የእግዚአብሔር ነቢይ አለ። ይህን ማየት የሚችሉ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው፣ ይህን የሚሰሙ ጆሮዎች ብፁዓን ናቸው፣ እናም ይህን ማመን የሚችሉ ብፁዓን ናቸው። ዮሐንስ 14:12 በእርግጥ በአገልግሎቱ ተረጋግጧል። ማጋነን አያስፈልግም፤ በተቃራኒው፡ በዚህ ትሑት የእግዚአብሔር ሰው እግዚአብሔር በሰጠው አገልግሎት የተከናወኑ አንዳንድ ነገሮችን ለመናገር አንዳንድ ሰው ሊፈራ ይችላል።

የመጨረሻው ዘመን መልእክት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር መቶ በመቶ የሚጣጣም መሆኑ መነገር አለበት። አንድ ሰው ወንድም ብራንሃም የተናገረውን ወስዶ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ደረጃ ላይ ካስቀመጠ፣ እንዲህ ያለው ሰው ይሳሳትል። የእግዚአብሔርን ጸጋ በበቂ ሁኔታ የተቀበለ እና የተማረውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማጣራት ያረጋገጠ ሁሉ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሚዛናዊነት ይኖረዋል።

የመጨረሻው ዘመን መልእክት ከዚህ ዘመን ጋር በተያያዘ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል እንጂ ሌላ አይደለም። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጨመረ ነገር አይደለም፣ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተገለጠ ቅዱስ ጽሑፍ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እውነተኛው ቃልና ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ንጹሕ ትምህርት ተመልሰዋል። በእርግጥም እነዚህን ሁሉ ነገሮች በአእምሮአችን ብቻ አውቀን መቀበል በቂ አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ምስክር መሆን አለብን። እነዚህን ነገሮች ወስዶ በአእምሮው ብቻ የሚያምን ማንኛውም ሰው፣ ሌሎችን ለማስተማር ቢሞክር ታላቅ ጉዳት ሊያደርግ ይችላል። ቃሉን በልባቸው የተቀበሉት ለሌሎች ታላቅ በረከት ሊሆኑ ይችላሉ።

በሐዋርያት ሥራ 20:25 እንዲህ እናነባለን (ጳውሎስ ሲናገር) ፦ “ አሁንም ቢሆን በመካከላችሁ ተዘዋዉሬ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሰብክሁላችሁ እናንተ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንደማታዩ አውቃለሁ። ስለዚህ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን በዚች ቀን እመሰክርላችኋለሁ፤የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና ፤ ምንም አላስቀረሁባችሁም።በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋዉ ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።” ጳውሎስ አስተማሪ፣ ሐዋርያና ነቢይ ነበር። የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ እንደሰበከ መናገር ችሏል። በአዲስ ኪዳን የነብይነት አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን ነቢያት አገልግሎት ጋር መመሳሰል አለበት፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለዘላለም ያው ስለሆነ።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ታላቁና ስለ አስፈሪው የጌታ ቀን አስቀድሞ ስለሚመጣው ነቢይ ብቻ ሳይሆን፣ ስለሚነሱ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያትም

እንደሚናገር እውነት ነው። የብሉይ ኪዳንን በጥንቃቄ ካነበብን፣ እውነተኛ ነቢይ **ጌታ እንዲህ ይላል** ብሎ በተነሳ ቁጥር፣ ትልቅ የሐሰተኛ ነቢያት ቡድን እውነተኛውን ነቢይ እንደተቃወሙ እናያለን። በኤርምያስ 23+26 ላይ እንደምናነበው በኤርምያስ ዘመን እንዲሁ ነበር። እውነተኛ ነቢይ የነበረው ሚክያስም እንደዚህ ሆነ፤ አራት መቶ ሐሰተኛ ነቢያት ተቃወሙት። ይህንን በ1ኛ ነገሥት 22 ላይ ማንበብ እንችላለን።

በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:1 ላይ በመጨረሻዎቹ ቀናት ነገሮች እንዴት እንደሚሆኑ እናነባለን። በ8ኛው ቁጥር ላይ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጻፈ፦ "ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደተቃወሙት፣ እንደዚሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው፣ ስለእምነት ረገድ ከንቱ የሆኑ ሰዎች ናቸው።" ይህ ደግሞ በዘመናችን የተፈጸመ ትንቢት ነው። ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ሙሴንና በዚያን ጊዜ የነበሩትን ተአምራት ሠራተኞች ለመጨረሻው ዘመን በማመልከት የጠቀሰው ለምንድነው? በዚያን ዘመንና እኛ አሁን እየኖርንበት ባለው ዘመን መካከል መመሳሰል ሊኖር ይገባል። ሁላችንም እንደምናውቀው ሙሴ እግዚአብሔር በእሳት ዓምድ ተገልጦለት የነበረው ነቢይ ነበር። በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም በሆነ እና በመጨረሻው ማረጋገጫ፣ ያው ጌታ ለወንድም ብራንሃምም በተመሳሳይ የእሳት ዓምድ ተገልጦለታል መባል አለበት። የጌታ መልአክም አነጋገረውና፦ "ሙሴ ሁለት ምልክቶች እንደተሰጡት፣ እንዲሁ አንተም ሁለት ምልክቶች ተሰጥተዉሃል" አለው።

የእግዚአብሔር ቃል አሁን ተነስተዉ ትላልቅ ምልክቶችንና ድንቆችን በሚያደርጉ ሰዎች እየተፈጸመ ነዉ ፤ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ኢያኔስና ኢያንብሬስ እንዳደረጉት እውነቱን ጥለዋል። እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ 7:21 ላይ የተናገረው መፈጸም አለበት፦ "በሰማያት ያለዉን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጅ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይድለም።"

ጥያቄውን መጠየቅ አለብን፦ እነዚህ ትንቢት የሚናገሩ፣ አጋንንትን የሚያስወጡ፣ ተአምራትን የሚያደርጉ፣ ሆኖም በዓመጽ ጸንተዉ የሚኖሩ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ቃላት የሙሉ ወንጌል አገልጋዮችን ይገልጻሉ ማለት ይቻላል? ማንም ሌላ አጋንንትን አያስወጣም፣ ተአምራትን አይሠራም፣ ትንቢት አይናገርም እንዲሁም ሙሉ ወንጌልን አናምናለን አይልም። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል ያውጃል፦ "በሰማያት ያለዉን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጅ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይድለም።" ባደረግነው ነገር ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አንችልም፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ አለብን።

በዕብራውያን 10:35-37 ላይ እንዲህ እናነባለን፦ "ስለዚህም ታላቅ ዋጋ ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድረጋችሁ

የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኂልና። ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነዉ ፤ ሊመጣ ያለዉም ይመጣል አይዘገይም።"

በሉቃስ 7:29-30 መሠረት፣ የዮሐንስን መልእክት ያመኑ ሁሉ ተጠመቁና በእግዚአብሔር ፊት ጸደቁ። በወንድም ብራንሃም አገልግሎት እዉነተኛዉ የዉሃ ጥምቀት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደተሰበከ እናውቃለን። እዚህ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘመኑ ጸሐፍትን የጠየቀውን ተመሳሳይ ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን። በሉቃስ 20:4 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው?"

ስለዚህ እንጠይቃለን፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያለው ጥምቀት የእግዚአብሔር ነው ወይስ የሰው? ሕዝቡ ዮሐንስ ነቢይ እንደሆነ ያውቁ ነበር። በተመሳሳይ ሕዝቡ ወንድም ብራንሃም ነቢይ እንደሆነ ያውቁ ነበር። አሁን የመናገር ጊዜ ነው። ዝም የምንለው ለምንድነው? እዚህ ላይ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያለው የውሃ ጥምቀት በእግዚአብሔር ቃል **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለው መሆኑን መናገር አለብን። እባካችሁ ይህን አስፈላጊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በራሳችሁ ግንዛቤ ከእንግዲህ ወዲህ በተሳሳተ መንገድ አተርጉሙት፣ ይልቁንም፣ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት የተነገረውን ብቻ ተናገሩ። ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 2:38 ለአይሁድ ተናገረ፣ ፊልጶስ በሐዋርያት ሥራ 8:16 ለሰማርያውያን ተናገረ፣ እና ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 19:5 ለአሕዛብ ተናገረ። እዚህ ላይ ሦስት ምስክሮች አሉን። የሰዎችን ባሕል ተከትለን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ ትምህርትን እንዴት ችላ ልንል እንችላለን?

ወንድሞች ሆይ፣ ማንኛውም ትምህርት አጠያያቂ ከሆነ፣ መልሳችንን ለማግኘት የእግዚአብሔርን ቃል ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ መውሰድ አለብን። የባህላዊ ትምህርቶቻችንን ትተን የተረጋገጠ ነቢይ የእግዚአብሔርን ቃል በመለኮታዊ መገለጥ እንደተናገረ መቀበል ከቻልን፣ ነገሮች ይለወጣሉ። ማንም ሰው የእግዚአብሔርን እውነተኛ የተረጋገጠ ነቢይ ትምህርት ሊፈታተን ይችላልን? አንድ ሰው ነብይን በትምህርቱ ስህተት ሊሆን ይፍላል ብሎ አስቦ እና ራሱን ትክክል ነኝ ብሎ ሊያምን የሚችለው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ነብይን ችላ እንድንል አልላከልንም፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረታችንን እንድንሰጥ ፤እንድንጠነቀቅ ለማድረግ እና **ጌታ እንዲህ ይላል** የሚለውን እንድናምን ነው የተላከዉ። በኢሳይያስ 66:5 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- "በቃሉ የምትንቀጠቀጡ ሆይ ፤የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፡- የጠሉአችሁ ስለ ስሜም ያባረሩአችሁ ወንድሞቻችሁ፡- ደስታችሁን እናይ ዘንድ እግዚአብሔር ይከበር ብለዋል ፤እርሱ ግን ለደስታችሁ ይታያል፣ እነርሱም ያፍራሉ።"

በኢሳይያስ 48:3+5—6 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “ የቀደመዉን ነገር ከጥንት ተናግሬአለሁ፤ ከአፌም ወጥቶአል አሳይቼዉማለሁ፤ ድንገት አድርጌዉአለሁ ተፈጽሞማል፡፡…ስለዚህ፤አንተ ፡- ጣዖቴ ይህን አድርጓል ፤ የተቀረጸዉ ምስሌና ቀልጦ የተሰራዉ ምስሌ ይህን አዘዙኝ እንዳትል ፤ አስቀድሜ ነግሬሀ ነበር ሳይሆንም አሳይቸህ ነበር፡፡ ሰምተሃል፤ይህን ሁሉ ተመልከት፤እናንተም የምትናገሩት አይድላችሁምን? የተሰወሩትን ያላወቅሃቸዉንም አዲሶች ነገሮችን ከዚህ ጀምሬ አሳይቼሃለሁ፡፡ ኢሳይያስ 46:9—10 እንዲህ ይላል፡- “የቀድሞውን ነገር አስቡ፤ እኔ አምላክ ነኝና ሌላ የለም፤ እኔ አምላክ ነኝና እንደ እኔ ያለ የለም፣ ከመጀመሪያው መጨረሻውን፣ ከጥንትም ገና ያልተደረጉትን ነገሮች የሚናገር፣ ‘ምክሬ ይቆማል፣ ፈቃዴንም ሁሉ አደርጋለሁ’ የሚል፡፡”

ወንድሞች ሆይ፣ ጥሪያችሁ ምንም ይሁን ምን፣ እባካችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ለመከተል ትሑት ሁኑ፡፡ ሁሉም የታተሙትን የወንድም ብራንሃም በርካታ ስብከቶችን እንዲያነብ ይገደዳል፡፡ በራእይ 1:20 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምስጢር፤ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው፤ ያየሃቸውም ሰባቱ መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡”

ሞትንና ሲኦልን ድል የነሳው በቀኝ እጁ ያሉ ሰባቱ ከዋክብት ለሰባቱ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ሰባቱ መልእክተኞች ናቸው፡፡ እነርሱም በሰው እጅ ወይም በድርጅት እጅ ውስጥ አይደሉም፣ ነገር ግን በጌታ በዚያ ታላቅ እጅ ውስጥ ናቸው፡፡

በራእይ መጽሐፍ፣ ምዕራፍ 2 እና 3 ውስጥ ሰባት ጊዜ “ለቤተ ክርስቲያን መልአክ… ጻፍ፣ … እነዚህን ነገሮች ይላል…” ተብሎ ተጽፏል፡፡ እንዲሁም ሰባት ጊዜ “ድል የነሳ…” እና “ጆሮ ያለው ይስማ፣ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን” ተብሎ ተጽፏል፡፡ ጠላትን ማሸነፍ ከፈለግን፣ ይህን እንዴት ማከናወን እንዳለብን ማወቅ አለብን፡፡ በራእይ 12:11 ላይ እንዲህ እናነባለን፡- “እነርሱም በበጉ ደምና በምስክር ቃላቸው አሸነፉት፤ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም፡፡” ቃሉ ምስክርነታችን ይሁን፣ እኛም ከደሙ በታች እንገኝ፡፡ በወደደን በእርሱ አማካኝነት ከአሸናፊዎች በላይ ነን፡፡

በማጠቃለያም፣ ሁሉንም በ2ኛ ጴጥሮስ 3:2 ቃላት ሰላም እንላለን፡- “በቅዱሳን ነቢያት አስቀድሞ የተነገረውን ቃል፣ እና በሐዋርያቶቻችሁም ያገኛችኋትን የጌታንና የመድኃኒትን ትእዛዝ እንድታስቡ በሁለቱ እያሳሰብኋችሁ ቅን ልቦናችሁን አነቃቃለሁ፡፡”

እንዲሁም፣ ከሮሜ 16:24—27 የጳውሎስ ቃላት ጋር፡- “የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን ፤አሜን፡፡ እንግዲህ እንደ ወንጌሌ

ስለ ኢየሱስም ክርስቶስም እንደ ተሰበከ ፤ከዘላለም ዘመንም የተሰወረዉን አሁን ግን የታየዉ በነቢያትም መጻህፍት የዘላለም እግዚአብሔር እንደ አዘዘ ለእምነት መታዘዝ ይሆን ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የታወቀዉ ምሥጢር እንደተገለጠ መጠን ሊያበረታችሁ ለሚችለዉ ፤ ብቻዉን ጥበብ ላለዉ ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን ፤ አሜን።

**የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ** መምጣት እጅግ በጣም ቀርቧል። ቀና ብላችሁ ተመልከቱ፣ ቤዛነታችን ቀርቧልና። ጌታን ለመገናኘት ዝግጁ ናችሁን? “አሜን፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ና” (ራእይ 22:20ለ) ብላችሁ መጸለይ ትችላላችሁን? የእግዚአብሔር ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

# ከዊልያም ብራንሃም ጋር በተያያዘ የኔ ምስክርነት

ወንድም ብራንሃም ወደ ጀርመንና ስዊዘርላንድ ለስብሰባ የመጣው እ.ኤ.አ በነሐሴ 1955 ነበር። በእነዚያ ቀናት እኛ እዚህ አውሮፓ ውስጥ ለማየት የታደልነዉ ነገር ቢያንስ በወንጌላትና በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተመዘገበው ጋር ተመሳሳይ ነበር። በእውነትም፣ ኃጢአተኞች በታላቅ የንስሐ ስሜት ከኃጢአታቸው ንስሐ ገቡ፣ ታማሚዎች በግልጽ ተፈወሱ፣ የታሰሩትም በእግዚአብሔር ኃይል ነፃ ወጡ። ጌታ በሕዝቡ መካከል ሲሠራ ያየነው ነገር እጅግ ደስታ አስከትሏል። ዓይነ ስውራን አይታቸዉን ተቀበሉ፣ ሽባዎች ዳኑ፣ እና ሁሉም ዓይነት ተአምራት ተከናወኑ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በስተቀር ማንም እነዚህን ሥራዎች መሥራት አይችልም ነበር ሊባል ይችላል።

ከመጀመሪያው አገልግሎት በኋላ፣ ከእርሱ ጋር ጥቂት ቃላት ለመለዋወጥ ይህን የእግዚአብሔር ሰው ማግኘት ፍላጎቴ ነበር። ከዚህ በፊት አይቼው አላውቅም ነበር እና ስለ እርሱም ሆነ ስለ አገልግሎቱ ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም፣ ነገር ግን በልቤ ውስጥ ይህን የእግዚአብሔር ሰው ካየሁት ቅጽበት ጀምሮ ጥልቅ ፍቅር ነበረኝ። ከዚያ የመጀመሪያ የእሁድ ምሽት አገልግሎት በኋላ በነጋታው ወደ ሆቴል ሄድኩ። እጅ ከመጨባበጣችን በፊት፣ እኔ በእንግዳ መቀበያው ዴስክ ላይ ቆሜ ሳለሁ ወደ እኔ እየጠቆመ፣ "የወንጌል አገልጋይ ነህ" አለኝ። ከዚያም ወደ ግራ ዞሮ፣ ባለቤቴ መግቢያው አጠገብ ቆማ ነበር፣ ወደ እሷ ጠቆመና፣ "ይህችም ሚስትህ ናት" አለ። ከዚያም አንዳችን ወደ አንዳችን ተጠጋግተን እጅ ተጨባበጥን።

እንዲህ ያለ ሰው አይቼ አላውቅም ነበር፤ እርሱ እጅግ ትሑት ከመሆኑ የተነሳ እኔ በራሴ ትህትና ማጣት እጅግ አፈርኩ። ለአጭር ጊዜ ተቀራርበን ከተጨዋወትን በኋላ፣ የእግዚአብሔርን በረከት ተመኝቶልን ተለያየን ። ከስፍራው በእንባ ወጣሁኝ፣ጌታን ስለምሕረቱና ቸርነቱ እያመሰገንኩኝ። ወንድም ብራንሃም ያልተለመደ ልዩ አገልግሎት እንዳለዉ በዚያ ጊዜ አወቅሁ፣ ነገር ግን እ.ኤ.አ በግንቦት 7 ቀን 1946 ዓ.ም. በጌታ መልአክ የተሰጠውን ልዩ ተልእኮ አላውቅም ነበር።

በስብሰባዎቹ ቀናት ሁሉ ያየሁት በእውነቱ እጅግ በጣም አስደናቂ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እንደገና ተደግሞ ነበር። የተሰበሰቡት ሰዎች ቁጥር ከአሥራ ሁለት እስከ አሥራ ስድስት ሺህ እንደሚሆን ይገመት ነበር። ይህ በማዕከላዊ አውሮፓ የእግዚአብሔር ታላቅ ጉብኝት ነበር።

በቀጣዮቹ ዓመታት ይህን የእግዚአብሔር ሰው ሲሰብክ ለመስማት እና እግዚአብሔር በተአምራዊ ሁኔታ ሲሠራ እና ቃሉን ሲያረጋግጥ ለማየት በውስጤ ጥልቅ ፍላጎት ተፈጠረ። ይህ ሰው የተናገረበት በእግዚአብሔር የተሰጠ ሥልጣን በእኔ ላይ ጥልቅ ስሜት ጥሎብኝ ነበር። ለዓይነ ስውሩ፡- "በጌታ

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እይታህን ተቀበል!" ሲለው፣ ያ ዓይነ ስውር ከዚያ ጀምሮ ዓይነ ስውር አልነበረም። በጋሪ ላይ ለነበሩት ሽባዎች፡- "በእግዚአብሔር ኃይል ተፈውሳችኋል... በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሱ... ጋሪያችሁን አንስታችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ!" ሲላቸው፣ እንዲሁ ሆነ። በዚህ ሰው የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ባዶውን አልተመለሰም፣ ነገር ግን የተነገረውን ሁልጊዜ ፈጽሟል። ከዚህ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ፣ እንዲህ ያለ መለኮታዊ ሥልጣን እና በጌታ ዘንድ እንዲህ ያለ ማረጋገጫ ያለው ሰው አይቼ አላውቅም።

እ.ኤ.አ በ1958 ዓ.ም.፣ በዳላስ፣ ቴክሳስ በተደረገው "የፈውስ ድምጽ" ጉባኤ ላይ ተካፍያለሁ፣ ምክንያቱም ሬቨረንድ ጎርደን ሊንሳይ ወንድም ብራንሃምን ዋና ተናጋሪ አድርጎ ስላስተዋወቀ ነበር። በዚህ ጊዜ ጌታ የዚህን የእግዚአብሔር ሰው ልዩ ትንቢታዊ አገልግሎት እንዳይ አደረገኝ። በሌሎቹ ወንጌላውያን ሁሉና በዚህ የእግዚአብሔር ነቢይ መካከል ያለውን ልዩነት ማየት አልከበደኝም። በስብሰባዎቹ በሦስተኛው ቀን ነበር፣ "አሁን ይህ ሰው ምን እንደሚያስተምር እና ምን እንደሚያምን ማወቅ አለብኝ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ አያለሁ" አልኩ። ስብከቶችን እየቀረጹ የነበሩ ወንድሞች ሊዮ መርሲየር እና ጂን ጎልድ፣ ሰባት ካሴቶች ሰጡኝ። በእነዚያ ስብከቶች የሰማሁት ለእኔ በጣም አዲስ ነበር፤ ብዙ ወሳኝ የመጽሐፍ ቅዱስ ጉዳዮች ተዳሰዋል። ይህ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገር ልቤ ይቃጠል ነበር። ለእኔ፣ መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ መጽሐፍ ሆነ። ከዚያ በኋላ፣ በጄፈርሰንቪል፣ ኢንዲያና፣ ዩ.ኤስ.ኤ. የተሰበኩትን ሁሉንም ካሴቶች ተቀበልኩ። የተቀረጹትን መልዕክቶች በመስማት ታላቅ መንፈሳዊ በረከቶች ተገኝተዋል።

ከዚያም የማልረሳው ቀን መጣ። የጌታን ኃይለኛና ዘልቆ የሚገባ ድምፅ ስሰማ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 2 ቀን 1962 ነበር። በጣም ጥሩ የጠዋት ንጋት ነበር። ሌሊቱ አልፎ ፀሐይም ልትወጣ ነበር። ወደ መስኮቱ ስመለከት፣ የጌታ ድምፅ ከላይ፣ ነገር ግን ከቀኝ በኩል መጣ፣ የሚከተለውን ቃል በትክክል በጀርመንኛ ቋንቋ በታላቅ ሥልጣን እየገለጸ፡- "ባሪያዬ ሆይ፣ ለዚህች ከተማ ያለህ ጊዜ በቅርቡ ያልቃል። ቃሌን ለመስበክ ወደ ሌሎች ከተሞች እልክሃለሁ።" ድምፁ ከቀኝ ስለመጣ ወደ ግራ ወደቅሁ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቀስ ብዬ ራሴን ማንሳት ቻልኩ። ከዚያ በኋላ ከሥጋዬ ወጥቼ በሌላ ልኬት ውስጥ ቆሜ፣ ተፈጥሮአዊ ሥጋዬንም አየሁ። እጆቼ ከጎኔ የተንጠለጠሉ ነበሩ፣ መዳፎቼ በመንፈሳዊው ዓለም ወዳለሁበት ተከፍተዋል። አፌን ከፍቼ ምላሼን ስሰማ ራሴን ማየት እችል ነበር፡- "ጌታ ሆይ፣ አይሰሙኝም። ሁሉም በብዛት አላቸውና አይሰሙኝም።" ለጥቂት ጊዜ ዝምታ ከሰፈነ በኋላ የጌታ ድምፅ እንደገና የሚከተለውን ቃል ተናገረ፡- "ባሪያዬ ሆይ፣ የሚሰሙህ ጊዜ ይመጣል። ምግብን አከማች... ታላቅ ረሃብ ይመጣልና። ከዚያም በሕዝብ መካከል ቆመህ ምግቡን ትሰጣለህ። የአካባቢ አብያተ ክርስቲያናትን አትመሥርት እንዲሁም የመዝሙር መጽሐፍ አታሳተም፣ ምክንያቱም ይህ የቤተ እምነት ምልክት ነው።" እነዚህ ቃላት

በእግዚአብሔርና በሰው ፊት እውነት እንደሆኑ እመሰክራለሁ። ጌታ የተናገረበትን ቃናና ትክክለኛ መንገድ እንኳ አስታውሳለሁ እና መድገም እችላለሁ። ድምፁን ስሰማ፣ በተለይ ሥልጣኑን አስተውያለሁ። ፍጹምና የመጨረሻ ትእዛዝ እንደሆነ አውቅ ነበር። ያ ድምፅ እንደገና ቢናገር፣ መላው ዓለም ይቆማል ብዬ አሰብኩ። የደስታ ስሜት ወይም መዝለል አልነበረም፣ ነገር ግን በጌታ ፊት አክብሮትና ፍርሃት ነበር።

ምግቡን ከማከማችት ጋር ተያይዞ አንዳንድ ነገሮች እንደ አትክልትና ዱቄት ተጠቅሰዉ ነበር። ስለዚህ፣ መጀመሪያ ላይ በተፈጥሮ ትርጉሙ እንደሆነ አምኜ ነበር። ነገር ግን በዚያው ዓመት ታህሳስ ወር ላይ፣ የልምምዴን ትርጉም በተመለከተ ከጌታ መልስ ማግኘት ወደሚገባኝ ቦታ ደረስኩ። ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ለመብረር እና ወንድም ብራንሃምን ስለእርሱ ለመጠየቅ ወሰንኩ። በሉዊስቪል፣ ኬንታኪ አየር ማረፊያ ስደርስ ለወንድም ብራንሃም ደወልኩ። በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ቢሊ ፖል ስልኩን አንስቶ ወንድም ብራንሃም እንደሄደና መቼ እንደሚመለስ እንደማያውቅ ነገረኝ።

ይህ ቅዳሜ ስለነበር እና ወንድም ብራንሃምን በሳምንቱ መጨረሻ ለማግኘት አስቤ ስለነበር በጣም ተስፋ ቆረጥኩ። በዚያ እሁድ ጠዋት፣ ለአገልግሎት ጄፈርሰንቪል ዉስጥ ወደ አለዉ ታበርናክል ሄድኩ። በድንገት አንድ ወንድም ትንቢት ተናገረና ያለአንዳች ምክንያት እንዳልመጣሁ፣ ነገር ግን ነቢዩን እንደማገኝ እና ማወቅ ያለብኝን ነገሮች እንደሚነገረኝ ተናገረ። ኦህ፣ ያ ሸክሙን ከእኔ ላይ አነሳው! ፓስተር ኔቪል ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ቃል እንዳካፍል ጠየቀኝ። በማግስቱ ወንድም ብራንሃም ተመለሰና በራሱ መኪና ከሉዊስቪል ከዋይኤምሲኤ ሆቴል ወሰደኝ። ሌሎች ሁለት ወንድሞች፣ ባንኮች ዉድ እና ፍሬድ ሶትማን፣ ወንድም ብራንሃም እየነዳ ሳለ ከኋላ ወንበር ተቀምጠው ነበር። አብረን እራት በላን ከዚያም ለእኔ ትልቅ ትርጉም ወዳላቸው ጊዜያት ቀረብን። ጠረጴዛው ላይ ቅድም የተጠቀሱት ሁለቱ ወንድሞች እርስ በርሳቸው ፊት ለፊት ተቀምጠው ነበር፣ እኔ ደግሞ ከወንድም ብራንሃም ፊት ለፊት ተቀምጬ ነበር።

ወንድም ብራንሃም በጀርመንና ስዊዘርላንድ ስለተካሄዱ ስብሰባዎች በመጥቀስ ዉይይት እያደረገ ነበር እና ቀጠለ ፣ በመጨረሻም እነዚህን ቃላት ለመናገር ዕድል እስካገኝ ድረስ፡- “ወንድም ብራንሃም፣ አንድ ነገር ልጠይቅህ እችላለሁን?” እነዚያ የተናገርኳቸው ብቸኛ ቃላት ነበሩ፣ እና ወንድም ብራንሃም ወዲያው መለሰ፡- “ወንድም ፍራንክ፣ ጌታ የተናገረህን ልንገርህ?” ወንድም ብራንሃም አገልግሎት ላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በተግባር ሲሰራ በብዙ ጊዜ ምስክር ሆኛለሁ። ነገር ግን የእኔ ተራ ሲደርስ ፈጽሞ የተለየ ነበር። ወንድም ብራንሃም ጌታ በሺህ የሚቆጠሩ ማይሎች ርቀት ላይ የነገረኝን ቃል በቃል፣ ጌታ በተናገረበት ትክክለኛ ቅደም ተከተል ደገመው። በዚህ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ

ስጦታ ንግግሬ እስኪጠፋኝ ድረስ በጣም ተደንቄና ተገርሜ ነበር፣ እናም ወንድም ብራንሃም ሲቀጥል ማዳመጥ ብቻ ነበር የቻልኩት።

ጌታ የነገረኝን ከነገረኝ በኋላ፣ ቀጠለና እንዲህ አለ፡- "ወንድም ፍራንክ፣ እንዳሰብከዉ ረሃቡ የተፈጥሮ ረሃብ አይደለም እና ምግቡም የተፈጥሮ ምግብ አይደለም።" እርሱም፡- "እግዚአብሔር ቃሉን የመስማት ረሃብ ይልካል፣ እና ልታከማቸው የሚገባህ ምግብ በቴፕ ላይ የተቀመጠው ለዚህ ሰዓት የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ነው።" ከዚያም ቀጠለና፡- "ምግቡን እያወጣህ የምትሰጥበትን ጊዜ የቀረውን ምግብ እስክታገኝ ድረስ ጠብቅ" አለ።

እንዲህ ያለ ልምድ በአንድ ሰው ላይ ምን ሊያደርግ እንደሚችል ማንም መግለጽ አይችልም። ለነቢዩ ዳንኤል መገለጦችን የሰጠው ያው አምላክ፣ ይህን መገለጥ ለወንድም ብራንሃም ሰጠው። የዚህ ቃለ ምልልስ በተደረገበት ጊዜ፣ ወንድም ብራንሃም ራሱ ምግብን እንዲያከማች ተልእኮ እንደተሰጠው አላውቅም ነበር፣ እርሱም በብዙ አጋጣሚዎች፣ በሰባተኛው ማኅተም መልእክት ውስጥም ጭምር እንደጠቀሰው። የጌታ ተልእኮ ምን እንደሆነ ካወቅኩ በኋላ፣ የእኔ ተራ እስኪደርስ ድረስ ለብዙ ዓመታት መጠበቅ ነበረብኝ። ያንን ውድ ምግብ የያዙትን ካሴቶች ሁሉ ተቀበልንና የምንችለውን ያህል አከማቸን።

ወንድም ብራንሃም ወደ ጌታ ከተወሰደ በኋላ፣ ከቀብር በኋላ ባለው ቀን፣ "የቀረውን ምግብ እስክታገኝ ድረስ ጠብቅ፣ ከዚያም የምግብ ማውጣት ጊዜ ይሆናል" የሚሉት ቃላት ትዝ አሉኝ። በዚያን ጊዜ፣ በተሰጠኝ የተረጋገጠ ተልእኮ መሠረት ምን ማድረግ እንዳለብኝ በፍጹም እርግጠኝነት አወቅሁ። በጄፈርሰንቪል ውስጥ አንድ የውስጥ ድምፅ፡- "አሁን ምግቡን የምታወጣበት ጊዜ ደርሷል" የሚሉትን ቃላት ደገመኝ። በዚያ ደረጃ ቀጥተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎት፤ እንደ ድኑት ዕቅድ አካል አላውቅም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በእርግጥ ያውቅ ነበር። በአሞጽ 8:11 መሠረት፣ የጌታን ቃል ለመስማት ረሃብ እንደሚልክ ቃል ገብቷል። በማቴዎስ 24:45—47 ደግሞ ጌታችን በተገቢው ጊዜ ስለሚሰጠው ምግብ ተናግሯል። ከቁጥር 36 ጀምሮ ያለው ርዕስ የሰው ልጅ መምጣት ነው። አሁን የቃሉ ሙላት ተገልጧል፣ ስለዚህም፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ የተዘጋጀ ምግብ እየሰጠን ነው። ሰውም እንደገና ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ ይኖራል።

በጉዳዩ ላይ በዝርዝር መግባት ባይቻልም፣ ተናጋሪው ጌታ፣ ለእኔ የተናገረውን ቃል በቃል ፈጽሟል። የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል፣ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ለጌታ ነቢይ ለውድ ተወዳጁ ወንድም ብራንሃም እንደተገለጠለት፣ በአውሮፓና በመላው ዓለም ላሉ ብዙ ሕዝቦች ትኩስ ምግብ ሆኗል። እርሱ ምግብን እንዲያከማች ተልእኮ ተሰጥቶት ነበር። እግዚአብሔር ረሃብን የመላክ ኃላፊነት ነበረበት፣ እኔ ደግሞ ያንን ለማከፋፈል ኃላፊነት አለብኝ። በ110 አገሮች ውስጥ ስለተከናወነው ነገር የግል ምስክር ነኝ፣ እናም ይህ

በእግዚአብሔር የተሰጠ መልእክት በዚህ ትውልድ ውስጥ በመላው ዓለም በእግዚአብሔር እውነተኛ ልጆች ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖና ውጤት ዘላለማዊነት ብቻ ይገልጣል።

በሚቻልበት መንገድ ሁሉ፣ ምግቡን ሰጥተናል። የወንድም ብራንሃም ስብከቶች ወደ ብዙ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። በእግዚአብሔር ጸጋ እርስዎን በማገልገል ደስ ብሎናል። ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ መሠረት በዘመናችን አሁን ምን እንደሚሠራ እንድትተዋወቁ ወስኗል። እርሱ ሥራውን ከሙሽራይቱ ቤተ ክርስቲያን ጋር ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ዝግጁ ነው። ሁላችንም በውስጡ ድርሻ ይኑረን።

ሌሎች እንደሚያደርጉት፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ጸንታችሁ ቁሙ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

በእርሱ ትእዛዝ

Bro. Frank



በዊልያም ብራንሃም ራስ ላይ የሚታየው የእሳት ዓምድ ምስል የተነሳው እ.ኤ.አ ጥር 24 ቀን 1950 ዓ.ም. በሂዩስተን፣ ቴክሳስ፣ ዩ.ኤስ.ኤ. ውስጥ ነው። በሬቨረንድ ብራንሃም ራስ ላይ ባለው ምስጢራዊ ብርሃን የተነሳ ፊልሙ ከሂዩስተን ዳግላስ ስቱዲዮ ወደ ዶ/ር ጆርጅ ጄ. ሌሲ፣ ለኤፍ.ቢ.አይ. የ"አጠያያቂ ሰነዶች መርማሪ" ዘንድ ተላከ። በፊልሙ በሁለቱም ገጾች ላይ ዘጠኙ መነጽር ምርመራ ተካሂዶ ነበር። ጆርጅ ጄ. ሌሲ ፊልሙ ፍጹም እውነተኛ መሆኑን አረጋገጠ፡- “በምርመራ የቀረበው ፊልም (ኔጌቲቭ) እንደገና አልተነካካም፣ ድብልቅም ወይም ሁለት ጊዜ የተጋለጠም ፊልም አይደለም ብዬ ትክክለኛዉን አስተያየት እሰጣለሁ። በራሱ ላይ እንደ ሃሎ (ክብ ብርሃን) ሆኖ የሚታየው የብርሃን ጭረት የተከሰተው ብርሃን ፊልሙን በመምታቱ ነው።”

ይኸው ደራሲ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለሚናገሩባቸው በጣም ጠቃሚ ርዕሰ ጉዳዮችን ተመለክቷል። እነዚህ ብሩሹሮች በዓለም ዙሪያ በብዙ የተለያዩ ቋንቋዎች ታትመው ለብዙ ሰዎች ዘላቂ በረከት ሆነዋል።

እኛም በዚህ የሚሲዮን ማዕከል 21 የዊልያም ብራንሃምን የተስተካከሉ ስብከቶች አሳትመናል፤ እነዚህም እንዲላኩላቸው ለሚፈልጉ ሁሉ በጠየቁት ጊዜ ሊላኩ ይችላሉ። ያሉትን የሕትመቶች ዝርዝር ማቅረብ ይቻላል።

ውዱ ጌታችንና መድኃኒታችን ለራሱ ወገኖች ምን ዓይነት መንፈሳዊ ምግብ እንዳዘጋጀ ስታውቁ ትገረማላችሁ።

ፍላጎት ካላችሁ፣ ከዚህ በታች በተዘረዘረው አድራሻ መጻፍ ትችላላችሁ፡-


የሚሲዮን ማዕከል

ፖ.ሳ. ቁጥር 100707

47707 ክሬፈልድ፣ጀርመን

ኢሜል፡ volksmission@gmx.de ወይም

E.Frank@freie-volksmission.de

ድህረ-ገፅ፡ http://www.freie-volksmission.de